## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገድና ድልድይ ጥገና አፈፃፀምን በተመለከተ የተከናወነ

## የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት


**አዲስ አበባ**

**መጋቢት 2011 ዓ.ም**

# ማውጫ


**ማውጫ** ..........................................................................................................................................I

**የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (EXECUTIVE SUMMARY)** .......................................I

**ክፍል አንድ** ......................................................................................................................................1

መግቢያ ..............................................................................................................................................1

የባለሥልጣኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ሥልጣን፡- ..........................................................................2

የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር ...............................................................................................3

የባለሥልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል ....................................................................5

የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ .............................................................................................................................6

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (POTENTIAL AUDIT AREA) ........................................................7

የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች ........................................................................7

የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ......................................................................................................................8

የመንገድ ጥገና የሥራ ሒደት መግለጫ (PROCESS DESCRIPTION). .........................................................8

**ክፍል ሁለት** ....................................................................................................................................10

**የኦዲት ግኝቶች** ...............................................................................................................................10

*የመንገዶችና የድልድዮች ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት (Condition Servey) በየዓመቱ ስለመከናወኑ፦* ...........................10

*የድልድዮች ጥገና በስትራቴጂክ ዕቅድ እየተያዘ በየዓመቱ በዕቅድ ተይዞ መከናወኑን በተመለከተ፦* ......................11

*የመንገዶችና የድልድዮች ጥገና የሚከናወነው በእቅድ ላይ በተያዘው በጀት፤ ጊዜና በሚፈለገው ጥራት መሆኑን በተመለከተ፣* ...........13

*የመንገዶችና ድልድዮች በተፈቀደላቸው የክብደት መጠንና በሚያስተናግዱት የትራፊክ መጠን መሰረት መደበኛ ጥገና መከናወኑን በተመለከተ፣* .......................................................................................................................................20

*የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን በተመለከተ፦* ..........................................22

*የመንገድ ጥገና የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች የሚመረጡበት ሁኔታ በተመለከተ፦* ...............................................24

*ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ውሎች ተዘጋጅቶ በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፦* ....................................25

*ህብረተሰቡ በመንገድ ጥገና ላይ ያለውን አመለካከት በተመለከተ* ......................................................................28

*በራስ ኃይል ስለሚከናወኑ ድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና የድልድይ ጥገና ሥራዎችን በተመለከተ፦* .....................29

*የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር የአፈፃፀም መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፦* ..........31

*ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድና ድልድይ ጥገና ኮንትራክተሮች ጋር በተገባው ውል መሠረት ውጤታማ ስለመሆኑ፦* .........33

*ከመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት መከናወኑን በተመለከተ፦* ..........................34

የመንገዶችና የድልድዮችን መረጃ ለመያዝ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል መኖሩንና መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ ተደራሽ ስለመደረጉ በተመለከተ፡- ...................................................................................................................35

**ክፍል ሦስት** ....................................................................................................................................37

**መደምደሚያ (CONCLUSION)** ..............................................................................................................37

**ክፍል አራት** .....................................................................................................................................40

የማሻሻያ ሃሳቦች ....................................................................................................................................................40

አባሪ 1 ROAD ASSET MANAGEMENT DDG ..........................................................................................................................1

አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ......................................................................................................................................2

አባሪ 3፡ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ኔትወርክ ማኔጅመት ዳይሬክቶሬት የፊዚካል ስራ አፈፃፀም እስከ መስከረም 30 2011ዓ.ም ..........................................................................................................................................................6

## የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና ማሻሻያ ሃሳቦች ማጠቃለያ (Executive summary)

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጠን የፌዴራል መንገዶችና ድልድዮች የጥገና እና እንክብካቤ ሥርዓት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን ለማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ይህን የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2008 እስከ 2011 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- የአዳማ አሰላ አስፋልት መንገድ በ2008 ዓ. ም ድንገተኛ ጥገና ቢከናወንም መንገዱ በጎርፍ ተቆርጦ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣
- ለግል ኮንትራክተሮች የተሰጡ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች የመንገድ ጥገና ሥራ ክንውንና ጥራት በተፈለገው ደረጃ እየተከናወነ አለመሆኑ፣
- መንገዶችና ድልድዮች ሊስተናግዱት ከሚገባው የክብደትና የትራፊክ ፍሰት በላይ የሚያስተናግዱ መሆኑን፣
- የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን ከመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ስራ ጋር የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ በዕቅድና በኮንትራት ውል ውስጥ ተካቶ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- የመንገድ ጥገና የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች የሚመረጡበት ግልጽ መመሪያና መስፈርት አለመዘጋጀቱ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነዱ መሰረት ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ውል መዋዋል ቢኖርበትም ያለውል የሚያሰራ መሆኑ፣

- ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ፈጣን የሆነ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መዋቅር (አደረጃጀት) ወይንም የተዘረጋ ሥርዓት የሌለው መሆኑ፣
- በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች የሚጠየቁበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣
- በመንገዶችና በድልድዮች ላይ የሚተላለፉ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ለማስከበር አጥፊዎች በመንገዱ ላይ ባደረሱት ጥፋት ልክ ለመጠየቅ የሚያስችል መመሪያ የሌለ መሆኑ

በመሆኑም

- ተገነንብቶ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ወደ መንገድ ሀብት የገቡ መንገዶችና ድልድዮች እንደሚያስተናግዱት የትራፊክ ፍሰት መጠን፣ እና የሚስተናግዱት የክብደት መጠንን ከግምት ያስገባ ክትትል በማድረግና ሲገነቡ ታሳቢ የተደረጉ የአገልግሎት ዓይነትና ጊዜ እንዲሰጡ አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያገኙ ሊደረግ እንዲሁም መደበኛ ጥገና በሚመደብላቸው በጀት፣ ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ መንገዱም ሆነ ድልድይ የጉዳት መጠን ተባብሶ ለመንገድ ግንባታ የሚውሎውን የሃገርቱን ሀብት ሣይጎዳ ሊጠበቅ ይገባል፡፡
- የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶች የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የሚረዱ በመሆናቸው የመንገዶችም ሆነ የድልድዮች ጥገና በሚታቀዱበትም ሆነ ውል በሚገባበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸውና አብረው ሊታቀዱ በማድረግ የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ሊደረግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ እንደየ ሥራው ባህሪይ ብቃት ያላቸው የሥራ ተቋራጮችን ለማግኘት የሚረዳ ግልፅ የሆነ መምረጫ መስፍርትና መመሪያ በማዘጋጀት እና በሚመለከታቸው አካላት በማፀደቅ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ በተቋራጮች አቅም ውስንነት የሚፈጠረው የሥራ ጥራትና መጓተት ሊቀርፍ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ለኮርፖሬሽኑ ለሚሰጣቸው እያንዳንዱ

የጥገና ሥራዎች ውል ሊዋዋልና ግልጽ የሆነ የተጠያቂነት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- የድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ጊዜ የማይሰጡና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚፈልጉ በመሆናቸው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የአደረጃጀት ወይንም ሥርዓት በመዘረጋት ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ በማመቻቸት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎችን ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀትና ከሚመለከታቸው የአካባቢ መስተዳድሮች ጋር የጋራ ግንዛቤ በመያዝ የመንገድ ሀብት የሚጠበቅበት ምቹ ሁኔታ ሊኖር ይገባል፡፡
- የመንገድ ሀብት ለመጠበቅ እንዲረዳ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር  እየተዘጋጀ ያለው ደንብ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንዲገባ በማድረግ ከክብደት ጋር ተያይዞ በመንገድ ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሊቀንስ ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ኢትዮጵያ ለምጣኔ ሀብታዊ እድገቷ ወሳኝ ነው ብላ ትኩረት ከተሰጣቸውና በስፋት ከሚከናወኑ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶች የመንገድ ዘርፍ በግንባር ቀደምነት ይጠቀሳል፡፡ የመንገድ ዘርፍ ለኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት መፋጠን ፋይዳው ባሻገር፣ ሀገራት የደረሱበት የእድገት ደረጃ ማሳያም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

2. የመንገድ አውታር ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት አስፈላጊ ከሆኑትና ከዋንኞቹ አንዱ እንደመሆኑ መጠን ጥበቃና እንክብካቤ የሚያሻው የሀገር ሀብት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የመንገድ ርዝመት በየዓመቱ እየጨመረ እንደመጣ የሚታወቅ ሲሆን ይህ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰበት የመንገድ ሀብት ወቅታዊ ጥገና የማይከተለው ከሆነ ውሎ አድሮ ቅርፅ ያለው እርሻ መሬት ሊሆን እንሚችል መገመት አያዳግትም፡፡

3. እ.ኤ.አ. ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በሀገራችን በተከታታይ ተግባራዊ እየሆነ ያለው የመንገድ ልማት ፕሮግራም Road Sector Development program (RSDP) ብንመለከት እንኳን መንገዶችን ለማሻሻልና ለማስፋፋት ባለፉት 20 ዓመታት ብቻ እስከ 300 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ወጪ የተደረገ ሲሆን ይህን ያህል ገንዘብ ለፈሰሰበት የመንገድ አውታር ደግሞ ወቅታዊና ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ እንደሚገባ ግልፅ ነው፡፡

4. በሀገራችን ካሉት የመጓጓዣ ዘዴዎች የየብስ ትራንስፖርት ጠቀሜታ ድርሻ ከ95 በመቶ በላይ መሆኑ የመንገድ አውታሩን የማስፋፋት እና የማሻሻል ሥራን አስፈላጊነት እጅግ የጎላ አድርጎታል፡፡

5. የአውራ ጎዳናዎችን ለማሻሻል እና ለመጠበቅ እንዲሁም ድልድዮችን፣ ቦዮችንና የነበሩትን መንገዶች ለመጠገንና አዳዲስ መንገዶችን ለመገንባት ይቻል ዘንድ በንጉሰነግስት ቀዳማዊ ኃይለስላሴ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 115/1943 ዓ.ም አውራ ጎዳና በመባል ተቋቋመ፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ለውጥ ሂደቶችን በማለፍ የቀድሞ የአውራ ጎዳና ባለሥልጣን በ1970 ዓ.ም ከነበረበት የአውራ ጎዳናዎችን ከማስፋፋት ሥራ በተጨማሪ አዳዲስ የገጠር መንገዶች ግንባታ፣ የነበሩትንም ደረጃ የማሳደግ እና የመጠገን ሥራ እንዲያካትት ሆኖ በወቅቱ አገሪቱ ትመራበት በነበረው ርዕዮተ ዓለም መሰረት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 189/1972 በትራንስፖርት እና መገናኛ ሚኒስቴር ሥር እንደገና እንዲቋቋም

ተደረገ፡፡

6. ከሁለት ዓመታት በኋላም በአዋጅ ቁጥር 216/1974 የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሲቋቋም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንም በዚሁ ሚኒስቴር ስር ሆኖ የኢትዮጵያ ትራንስፖርት እና ኮንስትራክሽን በሚል አዲስ ስም የዋና ዋና የገጠር መንገዶችን ብቻ ሳይሆን የከተማ መንገዶችን፣ የአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳዎችን፣ ወደቦችንና የባቡር ሀዲዶችን የመሥራት ኃላፊነት ተረከበ፡፡

7. በ1983 ዓ.ም የኢትዮጵያ ትራንስፖርት ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ይባል የነበረው መ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 26/1983 እንደገና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተብሎ ዋና ተግባሩም የመንገድ ጥገናና ግንባታ ሆኖ ተጠሪነቱም እንደቀድሞው ለኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እንዲሆን ተደረገ፡፡ በ1985 ዓ.ም የተቋቋመው የሽግግር መንግስት አገሪቷ ከቀየሰችው የገበያ መር ኢኮኖሚ አንፃር የመ/ቤቱ ዋና ተግባር የመንገድ ጥገናና ግንባታ ላይ ብቻ እንዲያተኩር በማድረግ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 63/1985 በአዲስ መልክ እንዲቋቋም ተደረገ፡፡ መ/ቤቱን እንደገና ለማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በአዋጅ ቁጥር 80/1989 ተሻሽሎ የተቋቋመ፡፡

8. የኢትየጵያ መንገዶች ባለሥልጣን አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2003 መሰረት እንደገና የተቋቋመ ሲሆን በዚህ ደንብ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን አውራ ጎዳናዎችን ለማልማት እና ለማስተዳደር እንዲሁም በመንገዶች ወጥነትን ለማረጋገጥና የመንገድ አውታር በተቀናጀ መልኩ የሚያድግበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠርን ዋና ዓላማ አድርጎ ተቋቁሟል፡፡

## የባለሥልጣኑ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ ዓላማ እና ሥልጣን፡-

### ራዕይ

9. የኢትዮጵያ የመንገድ አውታር በ 2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ደረጃ በማድረስ የተገልጋዩን የላቀ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣

### ተልዕኮ

10. ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ አውታርን በጥራት፣ በወቅቱ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስፋፋት፣ በማሻሻል እና በመንከባከብ በሁሉም አካባቢ የሚኖረውን የኢትዮጵያ ህዝብ የመንገድ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግና ለአገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ትርጉም ያለው ድጋፍ መስጠት፡፡

ዓላማ

11. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

- መንገዶችን ማልማትና ማስተዳደር፣
- የመንገድ አውታር በተቀናጀ መልኩ የሚያድግበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር እና
- በመንገዶች ሥራ የደረጃ ወጥነትን ማረጋገጥ፣

ናቸው፡፡

## የባለሥልጣን መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

12. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 247/2003 መሰረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

- መንገዶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያመነጫል፣
- የመንገዶችን አመዳደብ መመሪያ ያወጣል፣ ብሔራዊ የመንገድ አውታርንና የመንገዶች ደረጃን ይመድባል፣ ይሰይማል፣ የመንገዶችን የዲዛይን ደረጃ ያወጣል፣
- የአገሪቱን የመንገድ አውታር አስመልክቶ የተቀናጀ ዕቅድ ያወጣል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤
- የአጭርና የረጅም ጊዜ የመንገድ ልማት ዕቅዶችንና ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ለመንገድ ሥራ የሚያስፈልጉትን ዲዛይኖችና የፊዚቢሊቲ፣ የአካባቢ ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤
- የመንገድ ሥራዎች እንዲከናወኑ ያስደርጋል፤ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በራሱ ኃይል የመንገድ ሥራዎችን ያከናውናል፤
- የሥራ እና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ ይዋዋላል፤ ሥራዎች በየውላቸው መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ይቆጣጠራል ወይም በሌላ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ያደርጋል፤
- አግባብነት ያላቸው የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ

የመንገዶችን ዲዛይን የሚሰሩ ወይም የቁጥጥርና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አማካሪዎችን እንዲሁም በመንገድ ሥራዎች ላይ የሚሠማሩ ሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበትን ዘዴዎች ይወስናል፤

- የመንገድ ሥራዎችን በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ጨረታ የሚከናወኑበትን አማራጭ ይወስናል፤
- የትራፊክ ደህንነት ምልክቶች እንዲዘጋጁና በመንገዶች ላይ እንዲኖሩ ያደርጋል፤
- የተሽከርካሪ ክብደት ደንቦችን በመንገዶች ላይ ያስከብራል፤
- ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም አስቸኳይ እርምጃ በመውሰድ መንገዱ አገልግሎቱን እንዲቀጥል ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ለሚመለከተው የመንግስት አካል ሪፖርት ያደርጋል፤
- መንገዶችን በሚመለከት ጥናትና ምርምር ያካሂዳል ወይም እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችም በሥራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤
- ከክልል የመንገድ ኤጀንሲዎችና አግባብነት ካላቸው ሌሎች አካላት ሲጠየቅ የምክርና የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፤
- ለመንገዶች ልማት የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል እንደአስፈላጊነቱ ያሰለጥናል፤
- መንገዶችን ከጉዳትና አለአግባብ ከመጠቀም ይጠብቃል፤ በመንገዶች ላይ የሚከሰቱ መሰናክሎችን ያስወግዳል ወይም እንዲወገዱ ያደርጋል፡
- ከመንገዶች ግራና ቀኝ ለሥራው የሚያስፈልገውን የመሬት መጠን ይወስናል፤
- ለመንገድ ሥራዎች እንዲሁም ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለመሣሪያ ማሳረፊያና ለሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልግ መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች ያለክፍያ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
- በሕግ መሰረት ለባለይዞታዎችና ለባለንብረቶች ካሣ በመክፈል ለመንገድ ሥራዎች የሚያስፈልግ መሬት ያስለቅቃል፤
- በመንገዶች ክልል ውስጥ የተገኙ ህገወጥ ንብረቶችን ያስነሳል፤
- በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውንም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች አግባብ ባለው ሕግ መሰረት እንዲጠየቁ ያደርጋል፤

- የመንገድ ሥራዎች በሚካሄዱበት ወቅት ለአካባቢ ጥበቃ የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎች ያደርጋል፤
- በክፍያ የሚያገለግሉ መንገዶችን ይወስናል፤ ከተጠቃሚዎች የሚሰበሰብ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤ ለመንገድ ፈንድ ገቢ ያደርጋል፤
- የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤
- ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## የባለሥልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅር እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

13. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በቦርድ የሚመራ ሲሆን በስሩ አንድ ዋና ዳይሬክተር ሲኖረው በዋና ዳይሬክተሩ ስር አራት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች እና አምስት የአገልግሎት ሰጪ ዳይሬክቶሬቶች የሚገኙ ሲሆን በአራቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ስር አስራ ስድስት ዳይሬክቶሬቶች ይገኛሉ፡፡ በአስራ ስድስቱ ዳይሬክተሮች ስር ደግሞ አርባ ሰባት የስራ ቡድኖች ይገኛሉ፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ሀብት አስተዳደር ዘርፍ ድርጅታዊ መዋቅር ሥዕላዊ መግለጫ **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

14. ባለሥልጣን መ/ቤቱ እስከ ጥር 1/2011 ዓ.ም 2289 ቋሚ እና 787 ኮንትራት በድምሩ 3076 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1050 ሴት እና 2026 ወንድ በጠቅላው 3076 ሰራተኞች ናቸው፡፡

### የፋይናንስ ምንጭ

15. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በእቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከመንግስት በየዓመቱ መደበኛና ካፒታል በጀት፣ ከብድር እና ከለጋሽ ድርጅቶች እርዳታ የሚያገኝ ሲሆን ከ2008-2010 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት መደበኛ፣ ካፒታል እና ከመንገድ ፈንድ በጀት፣ ያገኘው ብድርና እና የተሠጠው እርዳታ ውጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| የበጀት ዓመት | የበጀት ዓይነት | የፀደቀና የተስተካከለ በጀት (ብር) | ሥራ ላይ የዋለ (ብር) | አፈፃፀም በመቶኛ% |
|---|---|---|---|---|
| 2008 | መደበኛ | 209,000,000.00 | 209,000,000.00 | 100% |
| | ከመንገድ ፈንድ | 1,005,240,768.47 | 876,313,601.35 | 85% |
| | ካፒታል | 24,000,000,000.00 | 24,000,000,000.00 | 100% |
| | ከብድር | 9,000,034,000.00 | 9,000,034,000.00 | 100% |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 177,093,000.00 | -- | --- |
| | ጠቅላላ ድምር | 34,391,367,768.00 | 3,408,534,760,100 | 99.% |
| 2009 | መደበኛ | 235,747,000.00 | 235,747,000.00 | 100% |
| | ከመንገድ ፈንድ | 1,252,818,735.30 | 1,067,342,614.32 | 85.20 |
| | ካፒታል | 46,158,974,000.00 | 24,255,690,989.63 | 52.5% |
| | ከብድር | 11,000,000,000.00 | 4,200,000,000.00 | 38% |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 158,974,000.00 | 7,100,000.00 | 0.44% |
| | ጠቅላላ ድምር | 58,806,513,735.00 | 29,765,880,604.00 | 50.6% |
| 2010 | መደበኛ | 317,635,000.00 | 317,635,000.00 | 100 |
| | ከመንገድ ፈንድ | 1,455,372,587.48 | 1,213,899,361.78 | 83.41% |
| | ካፒታል | 35,000,000,000.00 | 22,848,102,404.02 | 65% |
| | ከብድር | 10,378,622,000.00 | 2,400,000,000.00 | 23% |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | 153,562,000.00 | 12,000,000.00 | 0.078 |
| | ጠቅላላ ድምር | 47,305,191,587.00 | 26,791,636,766.00 | 56% |
| 2011 ታህሳስ 30 ድረስ | መደበኛ | 329,000,000.00 | 151,889,945.63 | 46% |
| | ከመንገድ ፈንድ | 15,029,59966.00 | 451,577,521.78 | 30% |
| | ካፒታል | 27,900,000,000.00 | 157,523,67677.51 | 56% |
| | ከብድር | 10,387,307.00 | | |
| | ከለጋሽ ድርጅቶች | ---- | | |
| | ጠቅላላ ድምርደ | 29,731,959,966.00 | 16,355,835,145.00 | 55% |

## የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ

16. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸው የፌዴራል መንገዶችና ድልድዮች የጥገናና እንክብካቤ አፈፃፀም ለማሳደግ የማያስችሉ መሰረታዊ የአሰራር ሥርዓት ማነቆዎችን በጥናት በመለየት እና እንክብካቤው ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ የሆኑ ስልቶች ተነድፈው፣ ቁጥጥርና ክትትል ተደርጎባቸው ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ማነቆዎቹ ውጤታማ በሆነ መልኩ የተፈቱ እና የተተገበሩ መሆኑን ማጣራት ሲሆን፣ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ

ለይቶ ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡

## ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

17. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸው የፌዴራል መንገዶችና ድልድዮች የጥገና እና እንክብካቤ አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች እና መመዘኛ መስፈርቶች

**የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች** (Audit Issues)

18. ከላይ ለተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፡-

I. መንገዶችና ድልድዮች ከተገነቡ በኋላ ለረዥም ጊዜ ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ በአግባቡ ጥበቃ፤ ጥገና እና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑን መገምገም፣

II. መንገዶችና ድልድዮች ከተገነቡ በኋላ ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ የድልድዮችን ታሪክ(መረጃ) በተሟላ መልኩ በመያዝ ጥበቃ፤ ጥገና እና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑን መገምገም፣

III. ዘመናዊ፣ የተቀናጀና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመጠቀም ለሚፈልገው ተገልጋይ በብቃት እና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል እንዲሁም ቅንጅታዊ የአሰራር ስረዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት** (Evaluative Criteria)

19. ከላይ ለተገለጹትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 31 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህን የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የባለሥልጣን መ/ቤቱ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 247/2003፣ በውጤት ተኮር ሥርዓት (BSC) ማዕቀፍ የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ (2008-2012) ዓ.ም፣ Road Maintenance Technical Specification እና መልካም ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ተልከው

አስተያየት እንዲሰጥባቸው ተደርጓል፡፡ የተዘጋጀው መመዘኛ መስፈርት **በአባሪ 2** ተያይዟል፡፡

## የክዋኔ ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

20. ኦዲቱ የተከናወነው በአለማቀፉና በኢትዮጵያ ክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) እና ለመስሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ 2008 እስከ 2011 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ በፌዴራል መንገዶች ላይ የተከናወኑትን የመንገዶች እና የድልድዮ ጥገና አፈጻጸም የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

21. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ሲሆን በተጨማሪም በናሙና በተመረጡ ለመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት በዓለም ገና፣ ጅማ እና በነቀምት ዲስትሪክቶች በመገኘት ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና ማስረጃዎችን ጠይቆ በመከለስ እንዲሁም በናሙና በተመረጡ በዓለምገና ዲስትርክት የአዲስ ፍቼና ፍቼ ጎኃፅዮን እና አዳማ አሰላ፣ በጅማ ዲስትርክት ጅማ ጭዳ እና ጅማ በደሌ፣ በነቀምት ዲስትርክት በደሌ ነቀምት እና ነቀምት ጌድዮ የመንገዶች ጥገና ፕሮጀክቶች በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

## የመንገድ ጥገና የሥራ ሒደት መግለጫ (Process Description).

### ሀ. ጥገና የሚደረግላቸው መንገዶችን የመለየት፤

22. በየዲስትሪክቱ የሚገኙ የዲሰትሪክት ምህንድስና ክፍሎች በቀጠናቸው ያሉ የሚያስተዳድሩአቸውን መንገዶች በዓመት አንዴ በመቃኘት እና ክትትል በማድረግ የመንገዶቹን ይዘት እና ሁኔታ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ፤ ከትራፊክ ፍሰት እና የመንገዶቹን የብልሽት መጠን ወዘተ. በማጥናት ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የመለየት እና ምን አይነት (የመደበኛ፤ የወቅታዊ እና የተርም) ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው እና ለጥገና የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ግምት በማስቀመጥ ለባለስልጣኑ የመንገዶች አስተዳደር ክፍል እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

23. የቀረቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ የትኞቹ ቅድሚያ ይሰጣቸው የሚለው በባለስልጣኑ የመንገዶች አስተዳደር ክፍል ውሳኔ ከተሰጠበት እና ጥገና የሚደረግላቸው መንገዶች ከተለዩ በኋላ ለጥገና ሥራው ማስፈፀሚያ የሚሆን በጀት እንዲመደብ የመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤትን ይጠይቃል፡

### ለ. ጥገና እንዲደረግላቸው ኮንትራት የመስጠት፤

24. በባለስልጣኑ የቀረበው የበጀት ጥያቄ በመንገዶች ፈንድ ጽ/ቤት ተቀባይነት ሲያገኝ የመንገዱ ጥገና ሥራ ለተቋራጮች በጨረታና በገበያ ዋጋ በመደራደር ወይም እንደአስፈላጊነቱ በራስ ኃይል ለሚከናወን ሥራ በትእዛዝ የሚከናወንበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ የሚሠሩት የጥገና ሥራዎች በጥራት መሠራታቸውን የሚቆጣጠር አማካሪ ድርጅት የሚያስፈልግ ሆኖ ሲገኝ በባለስልጣኑ በኩል በተመሳሳይ በጨረታና በገበያ ዋጋ በመደራደር ይቀጠራል፡፡ የጥገና ሥራውን ለመሥራት እና የጥራት ቁጥጥር የማድረጉን ተግባር ለማከናወን ተቀባይነት ያገኙት የሥራ ተቋራጭ እና አማካሪ ድርጅቶቸ ሥራውን ከመጀመራቸው በፊት የሥራ ውል ከባለሥልጣኑ ጋር እንዲፈርሙ ይደረጋል፡፡

### ሐ. የመንገድ ጥገናው ተግባር በኮንትራቱ መሠረት መከናወኑን ክትትል ማድረግ፤

25. በኮንትራክተሩ በኩል የመንገድ ጥገና ሥራውን ለማከናወን ሊተገበር የሚችል የሥራ እቅድ መዘጋጀቱን፤ በመቀጠልም ለመንገድ ጥገናው ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለመደልደል የሚረዳ ቀመር በቅድሚያ ተዘጋጅቶ የግብዓቶች ድልድል መከናወኑን፤ የግብዓቶች ድልድል በቂ ካልሆነ ኮንትራክተሩ የማቴሪያል እና የመሳሪያዎች ግዥ/ኪራይ/ ስለመፈጸሙ፤ በቂ የሰው ኃይልም ስለመቀጠሩ በአማካሪ ድርጅቱ ተረጋግጦ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ከተደረገ በኋላ ለመንገድ ግንባታ በኮንትራክተሩ የተዘጋጁ ቁሳቁሶች እና የሰው ኃይል ወደ ሥራ ቦታ ያጓጉዛሉ፡፡

26. በኮንትራክተሩ የሚቀርቡ ለመንገድ ጥገና የሚያገለግሉ ግብዓቶች (materials) ጥራት በአማካሪ ድርጅቱ ከተረጋገጠ በኋላ እየተመረቱ ወደ ሥራ ቦታዎች እንዲጓጓዙ ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም በአማካሪ ድርጅቱ በኩል የመንገድ ጥገና ጥራት በእያንዳንዱ ሥራና ግብአት ላይ ክትትል እየተደረገ ኮንትራክተሩ የመንገድ ጥገና ፊዚካል ሥራዎችን ያከናውናል፡፡ የተሠሩትን የመንገድ ጥገና ሥራዎች መረጃ የያዘ ወርሐዊ የሥራ ክንውን የሚያሳይ ሪፖርት እና የክፍያ መጠየቂያ ተዘጋጅቶ ለአማካሪ ድርጅቱ ይቀርባል፤ የባለሥልጣኑ ተወካይ ማለትም አማካሪው በክፍያ መጠየቂያው ላይ ስለትክክለኛነቱ ከፈረመ በኋላ በግንባር በማቅረብ ወይም በፖስታ፣ በዲኤችኤል በመላክ ክፍያ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

### መ. የጥገና ሥራው ከተጠናቀቀ በኃላ ርክክብ ማድረግ እና መንገዱን መጠበቅ

27. በመጨረሻም በኮንትራቱ መሠረት የጥራት ደረጃውን ጠብቆ የተጠገነው መንገድ ባለሥልጣኑ በኮንትራት ስምምነቱ ላይ በተቀመጠው ስምምነት መሠረት በመረከብ እንዲያስተዳድር ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የመንገዶችና የድልድዮች ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት (Condition Servey) በየዓመቱ ስለመከናወኑ፡-

28. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸውን የመንገዶችና የድልድዮች ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት (Condition Servey) በየዓመቱ ሊያከናውን እና በአመታዊ እቅድ ተይዘው ጥገና እንዲደረግላቸው ሊያደርግ ይገባል፡፡

29. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

✓ የዳሰሳ ጥናት ስራቸው ከተከናወኑ የቆዩ ጥናቶች ሳይከለሱና ወቅታዊ ሳይደረጉ የጥገና ውል የሚገባ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የዓለምገና እና ነቀምት ዲስትሪክቶች የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ከተሰጠው ምላሽ ለማወቅ መቻሉን፣

ለማሣያ፡-

✓ አዲስ ፍቼ እና ፍቼ ጎሃ-ፅዮን ዲዛይን የተሠራው በ 2011 G.C ሲሆን ወደ ትግበራ የተገባው በ2016 G.C ነው፡፡
✓ ባኮ ሸንቡ እና ሸንቡ ፍንጫ ማዞሪያ በ2008 ዓ.ም የዳሰሳ ጥናት የተከናወነ ሲሆን በ2009 ዓ.ም መጨረሻ ይሄው ጥናት ሣይከለስ ወደ መንገድ ማሻሻያ (Up grading) የተካተተ መሆኑ፣

30. የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊዎች ለተላከላቸው በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) በሰጡት አስተያየት ፡-

✓ የአዲስ አበባ ፍቼ እና ፍቼ ጎሃ-ፅዮን መንገዶችን በተመለከተ የመንገዶቹ ላይ ምክረ ሀሳብ /ኦቨርሌይ/ ሥራ ለማከናወን ዲዛይን እንዲሠራ እ.ኤ.አ በ2011 ከአማካሪ መሀንዲስ ጋር የኮንትራት ውል የተፈረመ ቢሆንም መንገዱ መ/ቤቱ የዘረጋውን አዲሱን የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ሥርዓት ለመተግበር ከተመረጡ መንገዶች መካከል ስለነበረ የተከለሰ የዲዛይን ሥራ እ.ኤ.አ ታህሳስ 25 ቀን 2015 በአማካሪ መሀንዲሱ ቀርቦ በጫረታ የፍቼ ጎሃ-ፂዮን መንገድ የአማራ መንገድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ ሲያሸንፍ አዲስ አበባ ፍቼ መንገድ በተጫራቾች የቀረበው ዋጋ ከፍተኛ ስለነበረ ጫረታውን ለመሠረዝ የተገደዱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

31. የመንገዶችና የድልድዮች ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት (Condition Servey) እንደየመንገዱ ደረጃ፣ የመሬትና የአየር ንብረት (ፀባይ) ሁኔታ በጥናት በመለየት የዳሰሳ ጥናቱ

እና የዲዛይን ሥራው በየጊዜው በመከናወን ወቅታዊ ካልተደረገ፣ ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የተገነቡ መንገዶቹም ሆነ ድልድዮች ተበላሽተው የአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ አስተዋጽኦ ከማሳደሩም በላይ ባልተከለሱ ዲዛይን መሠረት ኮንትራቱን የሚቀበሉ የሥራ ተቋራጮችም ሥራውን በአግባቡ ለመፈፀም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡

## የድልድዮች ጥገና በስትራቴጂክ ዕቅድ እየተያዘ በየዓመቱ በዕቅድ ተይዞ መከናወኑን በተመለከተ፡-

32. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የድልድይ ጥገናን በተመለከተ ስትራቴጅክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በዓመታዊ ዕቅድ በመከፋፈል ሊተገበር ይገባል፡፡

33. ይሁን እንጂ፡-

- ✓ የድልድዮች ጥገናን በተመለከተ በስትራቴጅክ ዕቅድ ውስጥ ተካቶ ያልታቀደ መሆኑ፣
- ✓ ድልድዮች ለጥገና ልምድ ለሌላቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በመስጠት ከጥራት ጋር ተያይዞ የአፈፃፀም ችግሮች ያሉበት መሆኑን፣
- ✓ ከ2007 ዓ. ም ጀምሮ በ19 ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ሲከናወን የነበረው የድልድይ ጥገና ሥራ ከማህበራቱ ጋር የነበራቸው ውል በመጠናቀቁ በ2010 በጀት ዓመት ጥገና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የተለዩ 262 ድልድዮች ጥገና ያልተደረገላቸው መሆኑ፣
- ✓ በ2011 ዓ.ም ድልድዮች ጥገና ሥራን በተመለከተ በዓመታዊ ዕቅድ ተይዞ እየተከናወነ ስለመሆኑ ረቂቅ ሪፖርቱ እስከተዘገጀበት ጊዜ ድረስ ማስረጃ ያልቀረበ ቢሆንም ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት ምላሽ ላይ አባሪ አድርገው ባቀረቡት ማስረጃ ግን 333 ድልድዮችን ጥገና ለማከናወን በአመታዊ ዕቅዳቸው የያዙ መሆኑን የሚያሣይ ቢሆንም እስከ ጥር 30/2011 ዓ.ም የአንዱም ድልድይ ጥገና የተከናወነ የሌለ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለመንገድ ሀብት የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበው ቃለ-መጠይቅ ከተሰጠው ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ስለሁኔታው የመንገዶች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ተጠይቀው ፡-

- ✓ የድልድዮች ጥገና ሥራዎች በመ/ቤቱ በተዘጋጀ በኮምፒውተር በታገዘ የድልድይ አስተዳደር ሥርዓት ተሰብስበው የጉዳታቸው ቅደም ተከተል የሥራ መጠን ተዘጋጅቶ ለብቻ ዕቅድ ተይዞ እና በጀት ተመድቦ እየተሠራ መሆኑ፣

- ✓ የድልድዮች እና የጉልበት ተኮር ቀላል የመንገድ ጥገና ሥራዎች መንግስት ያስቀመጠውን የሥራ ዕድል ፈጠራ እና አቅም ግንባታ መሠረት በማድረግ ተገቢው ሙያዊ ሥልጠና ወስደው ልምድ ባላቸው መሐንዲሶች ክትትል እየተደረገ ሲሰራ የቆየ መሆኑ፡፡
- ✓ ሥልጠና ሣይወስዱ ወደ ሥራ የገቡ የሌሉ መሆኑና በሥራ ላይ የተፈጠረ ክፍተት አለመኖሩ፣
- ✓ የድልድይ ጥገናዎች ከሁን ቀደም ሲሰሩ በነበሩት ማህበራት በኮርፖሬሽኑ /ኢ.ኮ.ስ.ኮ/ በኩል በንዑስ ተቋራጭነት እንዲሰሩ በስምምነት ላይ መሆናቸውን፣
- ✓ በ2012 በጀት ዓመት በ2011 በጀት ዓመት ያልተጠገኑትን 262 ድልድዩች ጨምሮ በድምሩ 333 ድልድዩችን ለመጠገን ዕቅድ መያዙንና በዓመታዊ መርሃ ግብሩ መሠረትም ጥገናቸው የሚጀመረው በሁለተኛው አጋማሽ ዓመት መሆኑን፡፡

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልፀዋል፡፡ በስትራቴጂክ ዕቅድ ላይ ድልድዮች ጥገናን አስመልክቶ ለምን እንዳልታቀደ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

35. ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ቢሰጡም የድልድዮች ጥገና በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ ትኩረት ባለማግኘቱ በ2008–2012 ስትራቴጅክ ዕቅድ ውስጥ ታካቶ ያልታቀደ በመሆኑ፤ በ2010 በጀት ዓመት 262 ድልድዮች ጥገና ለማከናወን ታቅዶ ያልተከናወነበት ምክንያት ያልቀረበ መሆኑ፣ በ2011ዓ.ም በ2010 ታቅዶ ያልተከናወነ 262 ድልድዮችን ጨምሮ 333 ለመጠገን በዕቅድ መያዙን መረጃ ያቀረቡ ቢሆንም በረቂቅ ሪፖርቱ ላይ በሰጡት ምላሽ አያይዘው ባቀረቡት ማስረጃ ላይ መቼ እንደሚከናወን የሚያሳይ ባለመሆኑ እና ጥገናው እስከ 3ኛው ሩብ ዓመት ጥር 30/2011 ዓ.ም ያልተጀመረና (ክንውኑ 0%) በመሆኑና በወቅቱ እየተከናወነ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

36. የድልድዮችን ጥገና ለማከናወን ስትራቴጅክ ዕቅድ በማዘጋጀትና በዓመታዊ ዕቅድ በመከፋፋልና በዕቅዱ መሠረት ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ ረዥም ዕድሜ ያለቸው ድልድዮች የጉዳት መጠናቸው ሣይባባስ የሚጠገኑበት ምቹ ሁኔታ ካልተፈጠረ በውድ የሀገሪቱ ሀብት የተገነቡ ድልድዮች ከቁጥጥር ማነስ ለከፋ ጉዳት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡

**የመንገዶችና የድልድዮች ጥገና የሚከናወነው በእቅድ ላይ በተያዘው በጀት፤ ጊዜና በሚፈለገው ጥራት መሆኑን በተመለከተ፣**

37. በየዓመቱ የታቀዱት የጥገና እቅዶች በተያዘላቸው በጀት፤ ጥራትና ጊዜ ተጀምረው በወቅቱ እንዲጠናቀቁ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

38. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው የመንገድና የድልድይ የጥገና ስራዎች በታቀደላቸው ጊዜ ያልተጀመሩ፣ በእቅድ ተይዞ በተመደበላቸው በጀት፣ ጊዜና ጥራት ያልተጠናቀቁ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለምሳሌ፣

- ✓ የአዳማ አሰላ አስፋልት ኮንክሪት መንገድ ድንገተኛ ጥገና በማርካን ኃ/የተ/የንግ/ማህበር ከሐምሌ 20/2008 ዓ.ም /27/7/2016 እ.አ.ኤ/ እስከ መስከረም 20/2009 ዓ.ም (30/9/16 እ.አ.ኤ) ድረስ ተከናውኖ ቫትን ጨምሮ ብር 41,643,256.63 የተከፈለ ቢሆንም መንገዱ በጎርፍ ተቆርጦ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑን፣
- ✓ የአዳማ አሰላ አስቸኳይ መንገድ ጥገና ሥራው የሚጠናቀቀው በሁለት ወር ወስጥ ሲሆን የሥራ ማስጀመሪያ ደብዳቤ (Commencement Lettor) ሐምሌ 20/2008 /27/7/2016 እ.አ.ኤ/ እና የሥራ ዝርዝር (Work Order Given Date) ነሐሴ 2/2008 /02/08/16 እ.አ.ኤ/ ለማርካን ኃ/የተ/የንግድ ማህበር ተሰጥቶ የሥራ ትዛዝና የስራው ዝርዝር ከተሰጠው ከሁለት ወር ከሃያ ቀን በኃላ (ጥቅምት14/2009 ዓ.ም) ውል የተፈረመው መሆኑ፣





*ስዕል 1 እና 2 አዳማ- አሳላ መንገድ ጥቅምት 2011*

- ✓ ነቀምት ዲስትሪክት በ2009 የመንገድ ጥገና አንድ ከባድና አንድ ወቅታዊ፣ በ2010 ዓ.ም 9 ድልድዮች እና 3 የመንገድ መደበኛ ጥገና በዕቅድ ተይዘው ያልተከናወኑ መሆኑን፣
- ✓ በኮምቦልቻ ዲስትሪክት ደቡብ ወሎ ቦረና ወረዳና መካነ ሰላም ግንደ ወይን-ኮምቦልቻ መንገድ ከጥራት ችግር የተነሳ ያለጊዜው በከፍተኛ ደረጃ የተበላሸ በመሆኑ ህብረተሰቡ ችግር አለበት ብሎ ቅሬታ ያቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

39. በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ጥገና የሚያስፈልጋቸው መንገዶችን በመለየት ዕቅድና የሥራ ዝርዝር በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የሚሰጣቸው ቢሆንም መንገዶች በታቀዱት ዕቅድ መሠረት ጥገና የማያገኙ መሆኑ፣
    - ✓ በ2008 ዓ.ም መቱ - ጎሬ - ጋምቤላ፣ ደምቢ - በደሌ እና ሊሙ መገንጠያ - ኮሳ ሰቃ መደበኛ ጥገና ታቅዶ ያልተከናወኑ መሆኑ፣
    - ✓ በ2010 ዓ.ም በለጠ ጫካ - ጎጀብ ወንዝ፣ ጎጀብ ወንዝ - ቦንጋ፣ ጋምቤላ - አቦቦ እና ጋምቤላ - ሸበል መደበኛ ጥገና ታቅዶ ያልተከናወኑ መሆኑ፣
    - ✓ በጅማ ዲስትሪክት በ2010 በጀት አመት በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በኩል መደበኛ ጥገና እንዲከናወን የታቀደው 430 ኪ.ሜ. ሲሆን እስከ ጥቅምት 2011 ዓ.ም 127 ኪ.ሜ. /38%/ ብቻ ያከናወነ መሆኑ፣

40. ጥገና እንዲደረግላቸው በዕቅድ የተያዙት መንገዶች በጨረታ መዘገየት እና በዲዛይን ችግር ምክንያት በወቅቱ የጥገና አገልግሎት ያለገኙ መንገዶች መኖራቸው፤

ለማሣያ፡-

- ✓ በጨረታ መዘግየት ምክንያት በ2009 እና 2010 በጀት አመት ጋምቤላ - ሴክሽን መደበኛ ጥገና በሁለቱም ዓመት ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ✓ በ2008፣ 2009 እና 2010 በጀት አመት አዲስ-ጊቤ ወንዝ ከባድ መንገድ ጥገና ፕሮጀክት 3ቱም ዓመት በዲዛይን ችግር ምክንያት መንገዱ ሣይጠገን ቀርቶ ለከፍተኛ ጉዳት እየተዳረገ መሆኑ፣
- ✓ የታቀደዉን የጥገና ዓይነት/ደረጃ በማውረድ ጥገና የሚሰራ መሆኑ፣
- ✓ በተጨማሪ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ኔትወርክ ማኔጅመት ዳይሬክቶሬት የነባር ፕሮጀክቶች የፊዚካል ስራ አፈፃፀም እስከ መስከረም 30 2011ዓ.ም ድረስ ያለው **በአባሪ 3** ተያይዟል፡፡





*ስዕል 2 እና 3 ጌድዮ ባኮ መንገድ በወቅቱ ጥገና ባለመደረጉ መንገዱ ተብላሽቶ ለትራንስፖርት አገልግሎት አስቸጋሪ*
*መሆኑን የሚያሣይ*

*41.* ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት

ምላሽ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸውን በመግለፅ ስለሁኔታው በሰጡት አስተያየት፡-

- ✓ የአዳማ አሰላ መንገዱ በድጋሚ የተጎዳው በተሰራው የስራ ጥራት ችግር ሳይሆን በአካባቢው ያለው ደየአ የመስኖ ግድብ ውሃ ሞልቶ የመንገዱን ክፍል ስለጎዳውና በመንገዱ ላይ ይህን ከፍተኛ የሆነ ውሃ ማስተናገድ የሚችል ስትራክቸር ባለመኖራቸው ምክንያት መሆኑ፣
- ✓ በአዳማ-አሰላ መንገድ ላይ የደረሰው ጉዳት በጣም አደገኛ ከመሆኑ የተነሳ ችግሩ በተከሰተበት ሰዓት/ጊዜ የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የመስክ ጉብኝት በማድረግ የችግሩን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአስቸኳይ ሥራውን እንዲሠራ የሥራ ትዕዛዝ ቢሠጠውም በሚፈለገው ፍጥነት ወደ ሥራ መግባት ባለመቻላቸውና ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሥራውን ባለመሥራታቸው ከሥራው አንገብጋቢነት አኳያ ታይቶ በአቅራቢያው የአዲስ-ሞጆ-መቂ መንገድ ከባድ ጥገና ሥራን የሚያከናውነው ተቋራጭ ሥራውን እንዲሠራ መንገዱን በሚያስተዳድረው የመ/ቤታቸው የዓለምገና መንገድ ኔትወርክ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬት የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ሐምሌ 25/2008 ዓ.ም (እ.ኤ.አ ኦገስት 1/2016 ) የይሁንታ በማግኘቱ እና የኮንትራት ውሉ እስከሚፈረም ድረስ ሥራው ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ ሥራውን ለማስጀመር የተገደዱ መሆኑ፣
- ✓ በ2008 በጀት ዓመት የ5 ድልድዮች ጥገና ለማከናወን ቢታቀድም የግዢ ሂደት በመጓተቱ ምክንያት ሳይሰሩ የቀሩ መሆኑ፣
- ✓ በደቡብ ወሎ ቦረና የሚገኘው መካነሰላም ግንደ-ወይን ኮምቦልቻ 220 ኪ.ሜ መንገድ በአስፋልት ደረጃ (DBST) በሚገነባበት ወቅት በነበረ የጥራት ችግር በርካታ ቦታዎች ላይ ጉዳት የደረሰበት ቢሆንም ችግር ያለባቸውን 67 ኪ.ሜ የመንገድ ክፍል በመለየት በ2010 ዓ.ም የባሰባቸው ቦታዎችን በመምረጥ ጥገና የተደረገለት መሆኑ፤ ይህም በወቅቱ በኮርፖሬሽኑ /ኢ.ኮ.ስ.ኮ/ በጋጠመው የአስፋልት እጥረት የጥገና ሥራ ተቋርጦ የነበረ ሲሆን በተያዘው 2011 በጀት ዓመት ጥገናው የቀጠለ መሆኑ፣

42. በ2009 በጀት ዓመት የመንገድ ጥገና አንድ ከባድ እንድ ወቅታዊ ጥገና ያልተከናወነበት ምክንያት፡-

- ✓ አንዱ የከባድ መንገድ ጥገና መቀናጆ - አሶሳ በ2009 በጀት ዓመት መጨረሻ የውል ስምምነት በመፈረሙ፣ ኮንትራክተሩ በተያዘለት ጊዜ ወደ ስራ ባለመግባቱ ሥራው በ 2010 በጀት ዓመት እንዲከናወን የተደረገ መሆኑ፣
- ✓ ኮንትራክተሩ በተያዘለት ጊዜ ወደ ሥራ ላለመግባት መንስኤ የሆነው ለመንገድ ጥገና የሚያስፈልገው የድንጋይ ምርት በመቃቢላ ወረዳ ስለተከለከለ ይህን ችግር ለመፍታት በጣም ረዥም ጊዜ በመፍጀቱ ነው፤ ይህንንም ችግር ለመፍታት የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ቡድን እስከመላክ የተገደደበት ሁኔታ የነበረ መሆኑ፤
- ✓ ወቅታዊ መንገድ ጥገና ሸርኮሌ-አባይ ወንዝ ሲሆን ያልተከናወነበት ምክንያትም የግል ሥራ ተቋራጭ የግዢ ሂደት መዘግየት ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም ሥራው በ2010 በጀት ዓመት ተዘዋውሮ መከናወኑን፣
- ✓ በ2010 በጀት ዓመት 9 ድልድዮች ጥገና እና 3 የመንገድ መደበኛ ጥገና ያልተከናወነበት ምክንያት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሚመለከታቸው አካላት ተደራጅተው ሲመጡ አሰልጥኖ የጥገናውን ሥራ ለማከናወን ዕቅድ ቢይዝም ከሚያደራጁት አካላት የሚላኩ ሰነዶችን የማጣራት ስራ ዝርዝር ሂደት ረጅም ጊዜ በመውሰዱ መሆኑን፣
- ✓ የድልድዩችን ጥገና በተመለከተ በ2011 በጀት ዓመት ዕቅድ መሠረት ፕሮጀክቶቹ በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በኩል እንዲሰሩ ስምምነት ላይ በመደረሱ የማኅበራቱን ዝርዝር ወደ ኮርፖሬሽኑ በመላክ በእነርሱ በኩል ሥራው እንዲከናወን ለዚህም የተያዘ በጀት በማዛወር ሥራ ላይ እንዲውል በሂደት ላይ መሆናቸው፣
- ✓ በ2010 በጀት ዓመት ነቀምት-በደሌ እና መቀናጆ-ደንቢ ዶሎ ያሉት መንገዶች በ2010 በጀት ዓመት አጋማሽ ላይ ግንባታቸው አልቆ ርክክብ ከተፈፀመ በኃላ ጥገና ለማከናወን የታቀደ ዕቅድ ቢሆንም ግንቦታውን የሚያከናውነው ኮንትራክተር ተገቢውን ርክክብ በጊዜው ባለማድረጉ መንገዱን ተረክበው መደበኛ ጥገናውን ማከናወን ያልቻሉ መሆኑ፣
- ✓ ሌላኛው በሰው ኃይል መደበኛ ጥገና ዕቅድ ውስጥ የተያዘው መንገድ አሶሳ-ኩምሩክ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማደራጀት ጋር ተያይዞ ሥራውን ማከናወን ያልተቻለ መሆኑ፣

- ✓ የመደበኛ ጥገና ፕሮጀክቶች በዕቅድ የተያዙትም በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን በኩል ባጋጠመው የአቅም ማነስ፣ የአስፋልት ጥገና ማሽን እጥረት እና የአስፋልት (Bitumen) እጥረት በመኖሩ ምክንያት ያልተጠገኑ መሆኑ፣
- ✓ የመደበኛ ጥገና ሥራ በባህሪው ትንሽና የተበታተነ በመሆኑ ኮርፖሬሽኑ ሥራውን አከናውኖ የሚያገኘው ገቢ አነስተኛ በመሆኑ ለጥገና ሥራ አነስተኛ ፍላጎት በማሳየቱ መሆኑ፣
- ✓ የተቋራጭ ቅጥር የሚከናወነው የመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት በመሆኑ የግዢ አሠራሩ ያነሰ ዋጋን ላስገባ ተቋራጭ ፕሮጀክት እንዲሰጠው ስለሚያስገድድ ተቋራጮች ዋጋ ሰብረው የሚገቡ በመሆኑ በአፈፃፀም ወቅት የአቅም ማነስ ስለሚገጥማቸው የመንገድ ጥገና ክንውን ላይ አልፎ አልፎ ተፅእኖ ያሳደረ መሆኑ፣
- ✓ ከመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት የሚመደበው በጀት አነስተኛ ቢሆንም በተመደበው በጀት ልክ የሚከናወኑ ጥገናዎች በጥገና ስታንዳርድ (maintenance Technical specification) መሠረት መሆኑና ለሁሉም ፕሮጀክቶች አማካሪ መሀንዲስ ተቀጥሮ ክትትል ስለሚያደርግ የጥራት ችግር እንዳይከሰት ጥንቃቄ የሚደረግ መሆኑ፣
- ✓ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የአዲስ ጊቤ መንገድ እ.ኤ.አ በ2012 የኦቨርሌይ ሥራ ለማከናወን አማካሪ ቀጥሮ ዲዛይኑን ያሠራ ቢሆንም መ/ቤቱ አዲስ የመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ሲስተምን ለመተግበር ፕሮፖዛል አዘጋጅቶ ቦርድ በማስፈቀድ ወደ ሥራ ሲገባ በእቅዱ ውስጥ ከተካተቱት መንገዶች መካከል አንዱ ነበር፡፡ በመጀመሪያ ዲዛይን እንዲሰራለት የታሰበው በአንድ ሎት ብቻ ቢሆንም የመንገዱ ርዝመት ረጅም ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለአስተዳደር እንዲመችና የጥገና ሥራውን በተፈለገው ጊዜና ጥራት ማከናወን እንዲቻል በሁለት ሎት ተደርጐ የዲዛይን ሥራ በአማካሪ መሀንዲሱ ተከልሶ የቀረበ ቢሆንም አዲሱን ሲስተም ለመተግበር የተመረጡት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ለፕሮጀክቱ ያስገቡት ዋጋ ከፍተኛ በመሆኑ ጨረታው መሰረዙን፣
- ✓ ከዓለምገና እስከ ሰበታ ያለው የመንገዱ ክፍል ከከተማዎቹ ሥፋት አንፃር እና ከሚያስተናግዱት የትራፊክ ሁኔታ በመጀመሪያው ዲዛይን ሥራ ይህንን ችግር ሊቀርፍ ባለመቻሉ ዲዛይኑ እንደገና የ10 ኪ.ሜትሩ በከተማ

ስታንዳርድ እንዲሠራ ለአማካሪ መሀንዲሱ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ዲዛይኑ እንገደና ተሰርቶ ቀርቦ ግዢው በሂደት ላይ መሆኑንና መንገዱ አስፈላጊ ጥገና ያልተከናወነበት ምክንያት በዲዛይን ችግር ሳይሆን በተጠቀሱት ምክንያቶች መሆኑን፣ ገልፀዋል፡፡

43. የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ከላይ የተጠቀሰውን ምላሽ ቢሰጡም

- ✓ የአዳማ አሰላ መንገዱ በድ‌ጋሚ የተጐዳው በአካባቢው ያለው ግድብ ውሃ ሞልቶ የመንገዱን ክፍል ስለጎዳ እና ይህን ከፍተኛ የሆነ ውሃ ማስተናገድ የሚችል ስትራክቸር ባለመኖሩ ምክንያት የተከሰተ መሆኑን የገለፁልን ቢሆንም በመጀመሪያው ጥገናው ሲከናወን ይህን ታሳቢ አድርጎ ለምን እንደልተከናወነ የተገለፀ ባለመኖሩ፣
- ✓ አዳማ-አሰላ መንገድ ላይ ለደረሰው ጉዳት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአስቸኳይ ሥራውን እንዲሠራ የሥራ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ኮርፖሬሽኑ በሚፈለገው ፍጥነት ወደ ሥራ ገብቶ ባለመሥራቱ እና ለአንድ ዓመት ያህል ሲዘገይ ባለሥልጣኑ ተከታትሎ እርምጃ ስለመውሰዱ የተገለፀ ነገር ባለመኖሩ፣
- ✓ በ2008 በጀት ዓመት የ5 ድልድዮች የግዢ ሂደት በመጓተቱ ጥገናው ያልተከናወነ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም የመንገድ ጥገናው ዕቅድ ሲታቀድ ይህንንም ታሳቢ ማድረግ ስለነበረበት፣
- ✓ በ2009 በጀት ዓመት መቀናጆ-አሰሳ ከባድ ጥገና እና ሽርኮሌ-አባይ ወንዝ ወቅታዊ ጥገና ታቅዶ ያልተከናወነበት ምክንያት ኮንትራክተሩ በተያዘለት ጊዜ ወደ ስራ ባለመግባቱ እና የግል ሥራ ተቋራጭ የግዢ ሂደት በመዘግየቱ መሆኑን የተገለፀው ኮንትራክተሩ በውሉ መሰረት ሥራ እንዲጀምር በባለሥልጣኑም ሆነ በአማካሪው በኩል ክትትል ማድረግ ይቻል ስለነበረና ግዥውንም በዕቅድ መምራት ይቻል ስለነበር፣
- ✓ የመደበኛ ጥገና ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የአስፋልት ጥገና ማሽን እጥረት በመኖሩ ምክንያት ጥገናዎች በወቅቱ የማይከናወኑ መሆኑን የገለፁ በሆንም ሥራው ሲሰጠው ይህ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ስለነበረበት፣

የተሰጡትን ምላሾች ለመቀበል ያስቸግራል፡፡፣

44. በየዓመቱ የሚታቀዱት የጥገና እቅዶች በተያዘላቸው በጀት፤ ጥራትና ጊዜ እንዲከናወኑና እንዲጠናቀቁ ካልተደረገ መንገዶቹም ሆነ ድልድዮች ተበላሽተው

የትራንስፖርት ማስተጓጎል ከማስከተሉም በላይ መደበኛ ጥገና ባለመደረጉ በሚከተለው ጉዳት ለሌላ መንገድ ግንባታ የሚውለው የመንግስት በጀት ለከባድ መንገድ ጥገና እንዲውል በማድረግ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና ከማሳደሩም በላይ ከመንገዱ ተገቢውን አገልግሎት ባለማግኘቱ በህብረተሰቡም ላይ ቅሬታ ያሳድራል፡፡

## የመንገዶችና ድልድዮች በተፈቀደላቸው የክብደት መጠንና በሚያስተናግዱት የትራፊክ መጠን መሰረት መደበኛ ጥገና መከናወኑን በተመለከተ፣

45. ባለሥልጣን መ/ቤቱ መንገዶችና ድልድዮች ሊያስተናግዱት የሚችለው የክብደት መጠንና የትራፊክ ፍሰት ልክ እንዲያስተናግዱ በማድረግ መንገዱን በመደበኛ ጥገና እንክብካቤ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ይህን ለማድረግ በአመታዊ ዕቅድ በመያዝ በየዓመቱ መደበኛ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

46. ይሁን እንጂ

- መንገዶች በየጊዜው የሚያድገውን የትራፊክ ፍሰት እና የጭነት መጠን መነሻ በማድረግ በዓመታዊ ዕቅድ በመያዝ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት ያላቸውን መንገዶች በጥናት በመለየት በወቅቱ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ያልተደረጉ መንገዶች መኖሩን፣

47. በባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገዶቹ የጉዳት ዓይነትና መጠን ላይ ያተኮረ የጥናት ስራ (condition survey) ከማከናወን ባለፈ በየጊዜው የሚያድገውን የትራፊክ ፍሰትና፣ የጭነት መጠን መሠረት ያደረገ የጥገና ተሞክሮ የሌለው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት የዓለምገና እና የጅማ ዲስትሪክት ቅ/ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች ቃለመጠይቅ ቀርቦላቸው ከተሰጠው ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

*ስዕል 5 እና 6 ጊዜ ጅማ ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት በመኖሩና በወቅቱ የጥገና አገልግሎት ባለማግኘቱ ለከፍተኛ ብልሽት እየተዳረገ ያለ መንገድ*

48. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ምላሽ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸውን በመግለፅ ስለሁኔታው በሰጡት አስተያየት፡-

- ✓ የጥገና ሥራ የሚከናወነው መንገዶች በሚያስተናግዱት የትራፊክ መጠን፣ የአካባቢ አየር ሁኔታ እና የመሬት አቀማመጥ መሠረት መሆኑን፤
- ✓ እያደገ የሚሄደውን የትራፊክ ፍሳት መጠን ለማወቅ 237 የትራፊክ ቆጠራ ጣቢያዎች ያላቸው መሆኑንና በእነዚህ ጣቢያዎች በዓመት 3 ጊዜ ቆጠራ የሚያካሂዱ መሆኑንና ይህም ለ7 ቀን ቀኑን 12 ሠዓት ከዚህ ውስጥ ሁለቱን ቀን 24 ሠዓት ቆጠራ ሚከናውኑ መሆኑ፣
- ✓ በመንገድ ላይ የሚጓዙትን ተሽከርካሪዎች ጭነት ለመቆጣጠር 14 የሚዘን ጣቢያዎች ያሉ መሆኑና ይህም 24 ሠዓት የሚሠራ መሆኑ፣
- ✓ የበጀት ውስንነት ጋር ተያይዞ መንገዶች በመደበኛ እና ወቅታዊ ጥገና በማቆየት ወደ ደረጃ ማሳደግ ዕቅድ እንዲገቡ የሚደረግ መሆኑ፣
- ✓ በተጨማሪ በመንገድ ፈንድ ጽ/ቤት መመሪያ መሠረት መንገዶች ወቅታዊ ጥገና ካገኙ እስከ 3 ዓመት ማገልገል ያለባቸው ቢሆንም እንደ መንገዱ መሬት አቀማመጥ የአየሩ ሁኔታ እና በሚያስተናግደው የትራፊክ መጠን ከ3 ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ወቅታዊ ጥገና እንዲያገኙ የሚደረግ መሆኑን

ገልፀዋል፡፡

49. መንገዶችና ድልድዮች የሚያስተናግዱትን የትራፊክ ፍሰትና የክበደት መጠን መሰረት በማድረግ መደበኛ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ በዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ እንደ መስፈርት ተካቶ ካልተከናወነ መንገዶች በመበላሸት ላልታቀደ ወጪና ለትራንስፖርት ማስተጓጎል ከማድረጉም በላይ መንገዱ ለከፍተኛ ብልሽት ይዳርጋል፡፡

**የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን በተመለከተ፡-**

50. የተጎዱ መንገድ ዳር ምልክቶች፣ የመንገድ ቀለሞችና ምልክቶች ከመንገድ ጥገና ሥራ ጋር በእቅድ ተካተው የሚሰተካከሉት ሊስተካከሉ ወይም በአዲስ ሊተኩ ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ፡-

- ✓ የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን ከመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ጋር ተካተው የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ በዕቅድ ያልተያዙና በኮንትራት ውል ውስጥ ያልተካተቱ መሆኑ፤
- ✓ ለትራፊክ አደጋ ምክንያት የሆኑ የመንገድ ቦታዎች በ 2008 በጀት ዓመት 300 የነበረውን በ2012 ስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 20 ዝቅ ለማድረግ የታቀደ ቢሆንም የስትራቴጂክ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ በየዓመቱ በመከፋፈል በ2008፣ 2009፣ 2010 እና 2011 በጀት ዓመታት በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ ያልተያዘና ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ✓ በ2008-2012 ዓ.ም. በስትራቴጅክ ዕቅድ ላይ የተሟላ የትራፊክ ምልክትና መረጃ ያላቸው መንገዶች በ2008 በጀት ዓመት ከነበረበት 55% በ2012 ወደ 90% ለማድረስ ቢታቀድም ስትራቴጂክ ዕቅዱን መሠረት በማድረግ በየዓመቱ በመከፋፈል በ2008፣ 2009፣ 2010 እና 2011 በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ ያልተያዘና ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ✓ በአሁኑ ወቅት ለትራፊክ አደጋ ምክንያት የሆኑ የመንገድ ቦታዎች (Black spot) እና የተሟላ ምልክት ያላቸው መንገዶች ምን ያህል እንደሆኑና ሽፋኑ ስንት ፐርሰንት እንደደረሰ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃ ያልቀረበ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎችና በቀረበው ቃለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

52. ስለጉዳዩ የዓለም ገናና የጅማ ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬቶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፤

- ✓ በአመታዊ እቅድ ላይ የመንገድ ደህንነት ስራዎችን በሚመለከት አመታዊ በጀት የሚመደብ ቢሆንም ክንውን ላይ ክፍተቶች ያሉ መሆኑ፣
- ✓ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጅማ ዲስትሪክት የመንገድ ደህንነት ስራዎችን ለማከናወን የነጠላ ዋጋቸው አነስተኛ በመሆኑ ለመስራት ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ መሆን፣
- ✓ በቅ/ዳይሬክቶሬቱ በኩል በሁሉም የመንገድ ክፍሎች ላይ ያሉትን የመንገድ ደህንነት ሥራዎችን ጥናት በማድረግ አስፈላጊው የስራ መጠን ለዋና መ/ቤት ልከን ስራውን በግል ስራ ተቋራጮች ለማከናወን በአሁኑ ሰዓት በጨረታ ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ የመንገድ ደህንነት ምልክቶች ጥቅማቸውን ካለመረዳት አንዳንድ ኃላፊነት የጎደላቸው ሰዎች በመንቀል፤ በመንገድ ደህንነት ምልክቶች ላይ ጉዳት በማድረሳቸው የትራፊክ አደጋ በመንገዶች ላይ እየደረሰ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

53. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ምላሽ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸውን በመግለፅ ስለሁኔታው በሰጡት አስተያየት፡-

ቀደም ሲል የእነዚህ መንገድን ተነባቢ የሚያደርጉ ወሳኝ የመንገድ ክፍሎች በኢ.ኮ.ሥ.ኮ የሚከናወኑ የነበረ መሆኑ፤ ነገር ግን ከሥራዎቹ አንፃራዊነት አነስተኛ መሆን የኢ.ኮ.ሥ.ኮ ፍላጐት በመቀነሱ ከመደበኛ እና ወቅታዊ ጥገና ጋር ማከናወን ያልተቻለ በመሆኑ በራሳቸው በጀት ስለሚያስፈልጋቸው የጥገና በጀት ላይ ተፅዕኖ ስለሚያሳድሩ ባለሥልጣኑ ይህንን በመረዳት ለብቻ የዳሰሳ ጥናት በማከናወን ጨረታ አውጥቶ አሁን ቢያንስ የ5 ኔትወርኮችን ሥራ የሚሸንፉ የሥራ ተቋራጭ በመቅጠር ሂደት ላይ መሆናቸውና ይህ ሥራ ከተጠናቀቀ በኋላ የተሟላ መረጃ የሚያዝ መሆኑን የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በተላከላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ገልፀዋል፡፡

54. የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን ከመደበኛ የመንገድ ጥገና ስራ ጋር ተካቶ በወቅቱ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ካልተደረገ

ምልክቶቹን ለብቻ ለመትከል ተጨማሪ ጊዜና ገንዘብ ስለሚጠይቅ ምልክቶቹም በአፋጣኝ ካልተተከሉ ለትራፊክ አደጋ መከሰት የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

## የመንገድ ጥገና የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች የሚመረጡበት ሁኔታ በተመለከተ፡-

55. ባለሥልጣኑ የመንገድ ጥገና የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች የሚመረጡበት ግልጽ መመሪያና መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

56. ይሁን እንጂ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ እንደ ሥራው ባህርይ ብቃት ያላቸው የሥራ ተቋራጮች ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ መመሪያና መስፈርት አለመዘጋጀቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ የመምረጫ ግልጽ መስፈርት ባለመኖሩ

- ✓ በአሰላ ቦቆጂ- ዶዶላ መደበኛ የመንገድ ጥገና የሚያከናውነው Natcon BC በመንገድ ጥገና ልምድ የሌለው በመሆኑ በሥራው ጥራት ላይ ተፅዕኖ ያሳደረ መሆኑ (Lack of Road maintenance experience, the contractor failed to attain the requair quality of work), መገለጹ፣
- ✓ በLotus Constraction Plc ዶሎመና-ቢድሬ እና ብድሬ-ብታታ ሁለት የከተማ ውስጥ መንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች ግንቦት 8/2008 ዓ.ም ተጀምሮ ታህሳስ 2009 ይጠናቀቃል ተብሎ ውል የተገባ ቢሆንም እስከ መስከረም 2011 ዓ.ም ደሎመና ብድሬ 9% እና ብድሬ ብታታ 67% ብቻ የተከናወኑ የተከናወነ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት የባለሥልጣኑ የመንገድ ሀብት የሥራ ሂደት (Road Asset Progress) መገምገሚያ ማስረጃ በመከለስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

*57.* ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ምላሽ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸውን በመግለፅ ስለሁኔታው በሰጡት አስተያየት፡- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሁሉንም የመንገድ ሥራዎች የግዥ ፍላጎቶችን ለማከናወን የግዥ ኤጀንሲ መመሪያን የሚከተል ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የግዥ አፈፃፀም መመሪያን በመከተል የራሱ የውስጥ ስታንዳርዶች እና መመሪያ በመዘጋጀት እየሠራበት የሚገኝ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58. የመንገድ ጥገና ሥራዎች የግዥ ፍላጎቶችን ለማከናወን የግዥ ኤጀንሲ መመሪያን በመከተል ግዥ የሚያከናውኑ ቢሆንም ግልጽ የሆነ የቴክኒክ መመዘኛና መገምገሚያ መስፈርት ስለመዘጋጀቱ እና በዚያ መመዘኛና መገምገሚያ መስፈርት

እየተጠቀሙ ስለመሆኑ የተገለፀ እና የቀረበ መረጃ ባለመኖሩ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያደግታል፡፡

59. ሥራ ተቋራጮች የሚመረጡበት ግልጽ የሆነ መመሪያና መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ካልተደረገ በመንገድ ጥገና ሥራ ላይ በቂ ልምድ እና አቅም የሌላቸው ስራ ተቋራጮች እንዲገቡ እና የመንገድ እና ድልድይ ጥገና ሥራው በተቀመጠለት የጥራት ደረጃ፣ በተፈለገበት ጊዜ እና በተያዘለት በጀት እንዳይጠናቀቅ የሚደርግ ከመሆኑም በላይ እንዲሁም ላልተገባ አሰራር በር እንዲከፈት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ውሎች ተዘጋጅቶ በውሉ መሰረት መከናወኑን በተመለከተ፡-

60. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ውሎችን በማዘጋጀት ሥራዎች በውሉ መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

61. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ያለ ውል በመግባቢያ ሰነድ (Memorandum of Understanding) ብቻ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የሚያሰራ መሆኑ ታውቋል፡፡ ነገር ግን መግባቢያ ሰነዱ ለእያንዳንዱ የጥገና ፕሮጀክት ውል መዋዋል እንዳለበት ቢገልጽም ባለሥልጣኑ ውል የማይዋዋል መሆኑ ታውቋል፡፡

62. ተወዳድረው ጨረታ አሸንፈው ውል ተዋውለው ወደ መንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ከገቡ የግል ሥራ ተቋራጮች ውስጥ የተወሰኑት

- በፕሮጀክት ጅማሮ ላይ በቂ ዝግጅት፣ ስኬጁል ዘግይቶና ያልተሟላ የመሣሪያ ስብጥር ማሠማራትና በሙሉ አቅም ሥራ ለመጀመር መቸገር፣
- የስራ ተቋራጩ ብቁ የሆኑ ባለሙያዎችን ያለመቅጠር ችግር እና
- የተቋራጩ አቅም ዉስንነት ተከትሎ ሥራቸው በውሉ መሠረት የማያከናውኑ መኖራቸው፣

ታውቋል፡፡ ለምሳሌ፡-

- ✓ መቂ-ሻሻመኔ እና ሻሻመኔ- አዋሳ ከባድ ጥገና በዮናታን አብይ አጠቃላይ የሥራ ተቋራጭ ጥገና እንዲያከናወን ውል የተገባው ግንቦት 23/2008 ዓ.ም (may 11/16) ተጀምሮ ሰኔ 16/2010 ዓ.ም (jun 23/2018) የሚጠናቀቅ ቢሆንም እስከ september 2018 ድረስ 1% ብቻ የተከናወነ መሆኑ፣

- ✓ አሰላ በቆጂ ዶዶላ መደበኛ (Routine Maintenance) በናቲኮን የሥራ ተቋራጭ ጥገና እንዲያከናወን ውል የተገባው ህዳር 27/2010 ዓ.ም (6-Noveber 2017) ተጀምሮ ህዳር 26/2012 ዓ.ም (6-Noveber 2019) የሚጠናቀቅ ቢሆንም ሥራው የተከናወነው 9% ብቻ በመሆኑ መዘገየት የሚታይበት መሆኑ፣
- ✓ በሻሻመኔ ዲስትሪክት ደሎመና ቢድሬ paving Town Section በLotus Constraction Plc ጥገና ለማካናወን ውል የተገባው ግንቦት 27/2008 (may 31/2016) ተጀምሮ ሰኔ 10/2009 (jun 17/2017) ይጠናቀቃል ቢባልም እስከ መስከረም 2011 (sebtember 2018) ድረስ 9% ብቻ የተከናወነ መሆኑን

በኦዲቱ ወቅት የመስከረም 2011ዓ.ም የመንገድ ሀብት የሥራ መገምገሚያ ሪፖርት በመከለስ ለማወቅ መቻሉ፡፡

63. ስለጉዳዩ በናሙና የታዩ ዲስትሪክቶች ቅርንጫፍ ዳይሬክቶሬቶች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣

- ከኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር ውል ባለመኖሩ :--
  - ✓ የሚሰጡትን ሥራዎች በጊዜ፣ በበጀት ልክና በሚፈለገዉ ጥራት ደረጃ እንዲያከናውን ለማስገደድ ካልሆነም እርምጃ ለመዉሰድ እንዳይቻል ውል ያለመኖሩ አንደኛው ክፍተት መሆኑን፣
  - ✓ በፕሮጀክት ደረጃ ስለማይገመገምና ሥራዉን ባለመፈጸሙ (ክፍያ ከመያዝና ሥራውን ቀምቶ ለሌላ ተቋራጭ ለመስጠት ከመሞከር ዉጪ) ተገቢዉን ቅጣት ለማስተላለፍ የሚያስችል አግባብ ባለመኖሩ ሥራዎችን መርጦ እንዲሰራ ዕድል የፈጠረለት መሆኑ፣
  - ✓ በተደጋጋሚ በሚቀርብ የወቅቱን ገበያ ሁኔታ ያገናዘበ የነጠላ ዋጋ ማስተካኪያ ይደረግልኝ ጥያቄ እና ሌሎች ቅሬታዎችን በዉል መሠረት ምላሽ ለመስጠት ባለመቻሉ ለሥራዉ ፍላጎት ማጣትና መስተጓጎል እንደ ምክንያት የተወሰደ መሆኑን፣

  ገልፀዋል፡፡

*64.* ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ምላሽ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸውን በመግለፅ ስለሁኔታው በሰጡት አስተያየት፡-

- ✓ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በተገነጠለበት ጊዜ የነበረውን የመግባቢያ ሠነድ (MOU)

መሠረት በማድረግ የሥራ ትዕዛዝ በመስጠት ብቻ ሥራዎች የሚከናወን መሆኑ ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በፕሮጀክት ደረጃ የዋጋ ድርድሮች በማከናወን ውል ለማሠር በመግባባት ሂደት ላይ መሆናቸውን፣

- ✓ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የኮንትራክተር ቅጥር የሚያከናውነው በመንግስት ግዢ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ መስፈርት መሠረት በመሆኑ በጨረታ ወቅት የተቋራጩ የመሣሪያ እና የሰው ኃይል መሟላት ታይቶ ውል የሚታሰር ቢሆንም የግዢ አሠራሩ አነስተኛ ዋጋ ላቀረበ ተጫራች ፕሮጀክት እንዲሰጥ ስለሚያስገድድ አልፎ አልፎ በአፈፃፀም ወቅት የአቅም ውስንነት የሚያጋጥማቸው ቢኖሩምም መ/ቤታችን ኮንትራክተሩ አፈፃፀሙን የማያሻሻል ከሆነ ውል እንዲቋረጥ የሚደረግ መሆኑ፤
- ✓ ለአብነትም ደሎ መና ቢድሬ paving Town Section ፕሮጀክት ውሉ ተቋርጧል፤ በአሁኑ ሰዓትም ስራው በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን እየተከናወነ መሆኑ፣
- ✓ በተመሳሳይ መልኩ መቂ-ሀዋሳ ፕሮጀክት ተቋራጭ በፕሮጀክቱ አካባቢ ላይ የሚገኘውን ብቸኛ የድንጋይ ካባ (stone quarry) የጠየቀ ቢሆንም ካባው ላይ ጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁበት በመሆኑ እስከ May 2017 ድረስ መስጠት ያልተቻለ መሆኑ፣
- ✓ ካባው ከተሰጠው በኋላ ተቋራጩ ድንጋይ መፍጨት የጀመረ ቢሆንም ቀጥሎ ወቅቱ ክረምት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለ4 ወራት ሥራውን መቀጠል ያልቻለ መሆኑ፣ በበጋ ወቅት አካባቢው ላይ የተፈጠረው የፀጥታ ችግር እና የውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ሥራው በተፈለገ መልኩ ለማከናወን አስቸጋሪ ሁኔታ የተፈጠረ ቢሆንም ኮንትራክተሩ ያለበትን የፕሮጀክት ማኔጅመንት ችግሮች ቀርፎ ሥራውን በተሻለ ሁኔታ እያከናወነ በመሆኑ ፕሮጀክቱ እንዲቀጥል የተደረገ መሆኑ
- ✓ እንዲሁም አሰላ-በቆጂ-ዶዶላ መደበኛ ጥገና ተቋራጭ በአካባቢው ላይ በነበረው የፀጥታ ችግር፣ ለአስፋልት ጥገና ሥራ የሚሆን መሣሪያዎችን ለማምጣት የውጭ ምንዛሪ እጥረት እና በኮንትራክተሩ በፕሮጀክት ማኔጅመንት ልምድ ማጣት ምክንያት ፕሮጀክቱ ዝቅተኛ አፈፃፀም ያስመዘገበ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ችግሮቹ ተቀርፈው አፈፃፀሙ በጥሩ ሁኔታ የሚገኝ በመሆኑ ፕሮጀክቱ እንዲቀጥል የተደረገ መሆኑን፣

65. የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ለሚያደርሱት የሥራ ግድፈት ውል ከማቋረጥ ውጪ ለተከሰተው ጉድለት ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ በመንገድ ጥገና ክንውኑ ላይ ተጠያቂነት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም የግል ሥራ የተቋራጭ በፕሮጀክት ጅማሮ ላይ በቂ ዝግጅት፤ ስኬጁል ዘግይቶና ያልተሟላ የመሣሪያ ስብጥር ማሠማራት፣ በሙሉ አቅም ሥራ ለመጀመር መቸገር፤ የስራ ተቋራጩ ብቁ የሆኑ ባለሙያዎችን ያለመቅጠር ችግር እና የተቋራጩ አቅም ዉስንነት ተከትሎ ሥራቸው በውሉ መሠረት የማያከናውኑ በመሆኑ የሰጡት መልስ አሳማኝ ሆኖ አልተገኘም፡፡

66. ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ውሎቹን በማዘጋጀትና ሥራዎች በውሉ መሠረት መከናወናቸውን ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ በየዓመቱ የሚታቀዱ የጥገና ዕቅዶችን በታቀደው መሠረት መፈፀማቸውን ገምግሞ ያለበቂ ምክንያት ባዘገዩት የሥራ ተቋራጮች ላይ ተጠያቂነትን ለማስፈን አዳጋች ከማድረጉም በላይ በወቅቱ ያልተከናወኑ መንገዶች የጉዳት መጠናቸው እየባሰ በመሄድ ለትራንስፖርት ማስታገጎልና ተጨማሪ የገንዘብና የጊዜ ወጪ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## ህብረተሰቡ በመንገድ ጥገና ላይ ያለውን አመለካከት በተመለከተ

67. ባለስልጣኑ የመንገድ ተጠቃሚው ህብረተሰብ በመንገድ ጥገና ላይ ያለውን አመለካከት ለማወቅ በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት በማከናወን እርካታው እንዲጨምር ሊሠራ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ተጠቃሚው ህብረተሰብ በመንገድ ጥገና ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅና ችግር ካለ የማስተካከያ (የእርምት) እርምጃ ለመውሰድ እንዲችል የእርካታ ዳሰሳ ጥናት ያላከናወነ መሆኑን ታውቋል፡፡

69. ስለሁኔታው የመንገዶች ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው ይህ ሥራ እስከ አሁን ያልተከናወነ መሆኑን እና ለወደፊቱ ግን የሚከናወን መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልፀዋል፡፡

70. ህብረተሰብቡ በመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ላይ ያላቸውን አመለካከት በጥናት በመለየት ከህብረተሰቡ የሚነሱ ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ በዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ምላሽ እንዲያገኙ ካልተደረገ ቅሬታው በየዓመቱ ከመጨመሩም በላይ ህብረተሰቡ በባለሥልጣኑ ላይ አመኔታ እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

**በራስ ኃይል ስለሚከናወኑ ድንገተኛ /አስቸኳይ/ የመንገድና የድልድይ ጥገና ሥራዎችን በተመለከተ፡-**

71. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች በራስ ኃይል ፈጣን የሆነ ምላሽ የሚሰጥበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል ፡፡

72. በኦዲቱ ወቅት ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች፡-

- በራስ ኃይል ፈጣን የሆነ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መዋቅር (አደረጃጀት) የሌለው መሆኑ፣
- በመንገድና ድልድይ ላይ ለሚከሰቱ ድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት ተብሎ እ.ኤ.አ በ2010 (2002 ዓ.ም) በእርዳታ ከጃፓን አገር የመጡ 11 የተለያዩ ተሽከርካሪዎች እና አንድ(1) የአስፋልት ፕላንት ያለ አገልገሎት የተለያየ ቦታዎች ላይ ቆሞ የሚገኙ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ከድንገተኛ ዳይሬክቶሬት ቃለ-መጠይቅ ቀርቦ ከተሰጠው ምላሽ እና ከቀረቡልን የሰነድ ማስረጃዎች በመከለስ ለማወቅ መቻሉ፣

73. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው እ.ኤ.አ በ2010 (2002 ዓም) በእርዳታ ከጃፓን አገር በእርዳታ የተሰጡት ተሽከርካሪዎች 14 ዳም ትራክ (የጭነት)፣ 2 የመስክ ኒሳን ስ/ዋገን እና 2 የመስክ ኒሳን ፒ/ካፕ ተሽከርካሪዎች ናቸው፡፡

- ✓ በዚህም መሠረት ከ14 የጭነት ተሽከርካሪዎች ውስጥ 5ቱ በደጀን ጎሃጺዮን መሬት መንሸራተት መከላከል ፕሮጀክት ላይ፣ 1 ጢቅ ሚዛን ጣቢያ ግንባታ ፕሮጀክት ላይ፣ 1 ዲማ ሚዛን ጣቢያ ፕሮጀክት ላይ፣ 1 በሚዛን ቦንጋ መሬት መንሸራተት መከላከል ፕሮጀክት ላይ፣ 1 አረቅጥ ከተማ ፉካ ክዳን ማልበስ ፕሮጀክት ላይ 3ቱ በአዲስ አበባ ዋናው መ/ቤት ቅጥር ጊቢ ውስጥ የአስፋልት ማልበስ ሥራ ፕሮጀክት ላይ እና 2ቱ በብልሽት ጋራዥ በጥገና ላይ ናቸው፡፡
- ✓ በተመሳሳይ 4ቱ የመስክ ተሽከርካሪዎች ከላይ በተጠቀሱት ፕሮጀክቶች ክትትል ሥራ ለማከናወን አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡
- ✓ የአስፋልት ፕላንቱን በተመለከተ ፕላንቱ ከተተከለበት ጊዜ ጀምሮ ለ1 ዓመት አገልግሎት ከሰጠ በኋላ ለተከታታይ 4 ዓመታት በአስፋልት ማቴሪያል ግብዓት እጦት ምክንያት አገልገሎት መስጠት ያልቻለ መሆኑን፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

74. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች በራስ ኃይል ፈጣን የሆነ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መዋቅር (አደረጃጀት) የሌለው በመሆኑ በምን መንገድ ሥራ ላይ እየዋሉ እንደሆነ ባለመገለጹ የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

75. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች በራስ ኃይል ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀትና መሣሪያ አዘጋጅቶ ዝግጁ ካልሆነ ችግሩ የደረሰባቸው አካባቢዎች ላይ ጉዳቱ ከመጨመሩም ሌላ ጨረታ አውጥቶ ድንገተኛ አደጋን ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ጥገናን ለማከናወን ስለማይቻል የኢኮኖሚና ማህበራዊ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር ሲሆን ባለሥልጣኑም ያለው ሀብት ሥራ ላይ ሳይውል ብክነት የሚያስከትል ሊሆን ይችላል፡፡

**በመንገዶች ላይ ጥበቃ መከናወኑን በተመለከተ፣**

76. በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቁ ለማድረግ የሚያግዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች የሚጠየቁበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

78. ሥርዓቱ ባለመዘርጋቱም :-

- ✓ መንገዶችን ተሽከርካሪ ማጠቢያ (ላቫያጅ)፤ መገበያያ፤ የግንባታ ቁሳቁስ ማከማቻና ማዘጋጃ ሆኖ ለተሽከርካሪ አደጋ በሚያጋልጥ መልኩ የሚገኙ መሆኑ ፤
- ✓ በጅማ ዲስትሪክት ከጅማ-ጊቤ ወንዝ፣ ከጅማ-ቦንጋ-ሚዛን እና ከጅማ- አጋሮ-በደሌ የመንገድ ኔትወርክ ላይ ቆሻሻ መድፋት፣ የሴንቴር(ፈሳሽ) ወደ ዲች መልቀቅና ከዲች ውስጥ ቆሻሻ ለማውጣት በሚደረገው ሂደት የዲች ክዳኖች (Dich Cover) እየተሰባበረና ከጥቅም ውጭ እየተደረገ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለመጠይቅ ከቀረበላቸው ዓለምገና፣ ጅማ እና ነቀምት ዲስትሪክት ከተሰጠው ምላሽ ለማወቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

79. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በቀረበላቸው መጠይቅ፣ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) እና በረቂቅ የኦዲት ሪፖርት ምላሽ በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩ ችግሮች መኖራቸውን በመግለፅ ስለሁኔታው በሰጡት አስተያየት፡-

መንገዶችን ከሰው ሠራሽ ጉዳቶች ለመጠበቅ የሚያስችል የውስጥ መመሪያ በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ እየተገመገመ መሆኑንና በበላይ አመራር ከፀደቀ በኋላ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

80. በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች የሚጠየቁበት ሥርዓት ተዘርግቶ ትግባራዊ ካልተደረገ ሰዎች በመንገድ ላይ የሚያከናውኑት ተግባራት ለትራፊክ አደጋ ከማጋለጡም በላይ በውስን የሀገሪቱ ሀብት የተገነቡ መንገዶች ለትራንስፖርት አገልግሎት መዋሉ ቀርቶ ለሌላ ተግባር እንዲውል በማድረግ ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

## የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር የአፈፃፀም መመሪያ መኖሩን በተመለከተ፡-

81. የመንገድ ሀብት ለመጠበቅ እንዲረዳ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር የአፈፃፀም መመሪያ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ በተዘጋጀውም መመሪያው መሰረት ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

82. ይሁን እንጂ በመንገዶችና በድልድዮች ላይ የሚተላለፉ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ለማስከበር አጥፊዎች በመንገዱ ላይ ባደረሱት ጥፋት ልክ የሚጠየቁበት አግባብ በደንብም ሆነ በመመሪያ ላይ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ስለሆነም

✓ መንገዶች መሸከም ከሚችሉት የክብደት መጠን እና የትራፊክ ፍሰት በላይ የሚያስተናግዱበት ሁኔታ መኖሩ በኦዲቱ ታውቋል፡፡ በዚህ ምክንያት ለተደጋጋሚና ከፍተኛ ጉዳት ከተጋለጡ መንገዶች መካከል፡-

- **በነቀምት ዲስትሪክት**፡- መንዲ-ዳለቲ፣ ነጆ-ሽመልቶኬ-ቤጊ እና ደንቢዶሎ -ሙጊ-ሸበል፣
- **በዓለም ገና ዲስትሪክት፡-**
    - ጀማ ድልድይ የሚገኘው (ለሚ -አለም ከተማ መንገድ ክፍል)
    - አዲስ - ቆሬ - ግቢ መንገድ

- አዲስ - አዳማ መንገድ
- አዳማ - አዋሽ መንገድ
- ሞጆ - መቂ - ዝዋይ መንገድ
- አለምገና - ቡታጅራ

የሚገኙ መሆናቸውን በኦዲቱ ወቅት ለዓለም ገና እና በነቀምት ዲስትሪክት ኃላፊዎች ለማወቅ መቻሉ፣

83. ስለጉዳዩ የፔቭመንትና ድልድዮች ዳይሬክተር ተጠይቆ በሰጡት ምላሽ ፤

✓ እስከ አሁን እየተሰራበት ያለው ደንብ ላይ ለድልድይም ሆነ መንገድ የተወሰነ ገደብ የሌለ አለመሆኑንና አሁን እየተጠና ያለው ጥናት ላይ ግን የተካተተ መሆኑ፣

✓ እስከ አሁን እየተሰራበት ያለው ደንብ የተሽከሪካሪዎች ጠቅላላ ክብደት ያልተቀመጠ መሆኑንና አሁን በተዘጋጀው ረቂቅ ድንብ ውስጥ ግን የተካተተ መሆኑ፣

✓ የክብደት መቆጣጠሪያ ላይ የመንግስት ህግ አጋዥ ሊሆን እና ግልፅ የሆነ መመሪያ ሊዘጋጅ የሚገባ መሆኑ፣

ገልፀዋል፡፡

84. ስለሁኔታው የመንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው መንገድን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለጉዳት ከሚዳርጉት ነገሮች አንዱ የተሽከርካሪዎች ክብደት ሲሆን ይህንንም ለመቆጣጠር የተሽከርካሪዎች ክብደትና መጠን መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር (11/1982) የሚጠቀምበት ቢሆንም የተጠቀሱት እና ተጨማሪ ክፍተቶች በደንቡ ላይ በመኖሩ ይህንን ለመቅረፍ ባለሥልጣኑ አማካሪ በመቅጠር ጥናት አከናውኖ የተሻሻለ ረቂቅ ደንብ እንዲፀድቅ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የላከና በማፅደቅ ሂደት ላይ ያለ መሆኑን እና ይህ ህግ ሲፀድቅ የቁጥጥር ሥርዓቱን የተሻለ ውጤታማ እንደሚያደረገው በኦዲቱ ወቅት በቀረበላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ገልፀዋል፡፡

85. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአማካሪ ድርጅት አስጠንቶ የሞተር ተሽከርካሪና ተሳቢዎችን ክብደት እና መጠን ረቂቅ ደንብ ላይ በቀን 29/09/03 ዓ.ም አስተያየት በማከል ወደ ትራንስፖርት ባለሥልጣን ያላኩ ቢሆንም ረቂቅ ደንቡ እስከ አሁን ለ8 ዓመት ያህል ተጠናቆ ሥራ ላይ ያልዋለ በመሆኑ የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

86. በመንገዶችና ድልድዮች ላይ የሚተላለፉ የተሽከርካሪዎች የክብደት መጠን ተወሰኖ የአፈፀፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ለቁጥጥርና ክትትል በሚያመች መልኩ ተግባራዊ ካልተደረገ አሠራሩ ለአድሎና ለሙስና የሚያጋልጥ ከመሆኑም በላይ አጥፊዎች በጠፉት ጥፋት ልክ ለመጠየቅ አዳጋች ያደረገዋል፤ መንገዱንም የበለጠ ለጉዳት ያጋልጠዋል፡፡

## ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድና ድልድይ ጥገና ኮንትራክተሮች ጋር በተገባው ውል መሠረት ውጤታማ ስለመሆኑ፡-

87. ባለስልጣኑ ከመንገድና ድልድይ ጥገና ኮንትራክተሮች ጋር በገባው ውል መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ የሚጠየቅበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ፡-

- ✓ ከወሰን ማስከበር እና ከካባ ድንጋይ ጋር ተያይዞ ለሚነሱ ችግሮች አፋጣኝ እልባት ባለማግኘታቸው በሥራ ላይ መዘግየትን እያስከተለ መሆኑ፣
- ✓ የ2011 በጀት በወቅቱ ፀድቆ ለዲስትሪክቶች ባለመላኩ እስከ 1ኛ ሩብ ዓመት ድረስ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን የድርጊት መር-ግብር አዘጋጅቶ ወደ ሥራ መግባት ያልቻለ መሆኑን፣

በኦዲቱ ወቅት ለጅማ እና ለነቀምት ዲስትርክቶች ቃለ-መጠይቅ ቀርቦ ከተሰጠው ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

89. ስለጉዳዩ የመንገዶች ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት አስተያየት፡-

- ለመንገድ ሥራ ግብዓት የሚውሉ ካባዎች ለተደራጁ ወጣት ማህበራት እና ለባሃብቶች እየተሰጡ በመሆኑ ከሦስተኛ ወገን ነፃ አድርጎ ለመጠቀም የወረዳዎች መስተዳደር አካላት ተባባሪነት ዝቅተኛ መሆናቸው እንደሆነ፣
- የ2011 በጀት ዓመት የመንገድ ጥገና በጀት ፀድቆ ለዲስትሪክቶች ያልተላከበት ምክንያት በጀቱ የሚፀድቀው በመንገድ ፈንድ በቦርድ በመሆኑና ቦርዱ በተለያዩ ምክንያቶች መሰብሰብ ባለመቻሉ እንደሆነ እና ሆኖም የጥገናው ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳደረ በመሆኑ ቦርዱ እስከሚሰበሰብ ድረስ ከፈንዱ ጽ/ቤት ጋር በመነጋገር ለ2010 በጀት ዓመት ላይ 20% በመጨመር ሥራው የሚከናወንበት ሁኔታ የተመቻቸ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

90. ኃላፊዎቹ ይህንን ምላሽ ቢሰጡም በመጀመሪያው የመንገድ ጥገና ዕቅድ ሲታቀድ እና ጨረታ ሲወጣ ለጥገና የሚውሉ ግብዓቶች ከማንኛውም ነገር ነፃ መሆኑን ተረጋግጦ ኮንትራት መገባት ሲገባ ኮንትራት ከተገባ በኃላ ከሦስተኛ ወገን ነፃ አድርጎ ለመጠቀም መታሰቡ በሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ እንዲሁም የ2011 በጀት ቦርድ ተሰብስቦ ባለማፅደቁ የተባለው የጥገና ዕቅድ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት መታቀድ የነበረበት በመሆኑ የተሰጠው ምላሽ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

91. የመንገድና ድልድይ ጥገና ኮንትራክተሮች በገቡት ውል መሠረት ግዴታቸውን እንዲወጡ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚጠበቅበትን ግዴታዎች ካልተወጣ በሥራ ላይ ለሚፈጠሩ ችግሮች ተቋራጮች እንደሽፋን ሊጠቀሙበት ስለሚችሉ ተጠያቂነትን ለማስፈን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡

### ከመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት መከናወኑን በተመለከተ፡-

92. ባለስልጣኑ የሚያስተዳድራቸው መንገዶች ከሚያልፉባቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት ሊያከናወን ይገባል፡፡

93. ይሁን እንጂ መንገዶች ከሚያልፉባቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት እንዲከናወን ያልተደረገ መሆኑን ታውቋል፡፡

94. ስለጉዳዩና ስለሁኔታው የመንገዶች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ተጠይቀው ለመንገድ ሥራዎች እና ተያያዥ ጉዳዮች ከመስተዳደር አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት ስትሪንግ ኮሚቴ እንዲዋቀር መመሪያ የተሰጠ መሆኑና በአጥጋቢ ደረጃ ባይሆንም እየተሠራበት መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልፀዋል፡፡

95. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በቅንጅት ለመሥራት ስትሪንግ ኮሚቴ እንዲዋቀር መመሪያ የተሰጠ መሆነና በአጥጋቢ ደረጃ ባይሆንም እየተሠራበት ነው በማለት የገለፁልን ቢሆንም በናሙና ተመርጠው በታዩት የዓለምገና፣ የጅማ እና የነቀምት የዲስትሪክት ዳይሬክቶሬቶች ይህ ሥራ ያልተከናወነ መሆኑን የገለፁ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

96. መንገዶች ከሚያልፉባቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት በማከናወን ከተለያዩ ቦታ ወደ መንገድ የሚፈሱውን የውሃ

አከላት እንዲከላከል እንዲያግዝ ካልተደረገ መንገዶች በውሃ በመጎዳት ያለ ጊዜ ለብልሽት ሊደረጉና ለተጨማሪ የጥገና ወጪ ሊዳርጉ ይችላሉ፡፡

የመንገዶችና የድልድዮችን መረጃ ለመያዝ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል መኖሩንና መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ ተደራሽ ስለመደረጉ በተመለከተ፡-

97. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸውን የመንገዶችና የድልድዮችን ታሪክ የሚይዝ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከልና መረጃውን ለሚፈልጉት አካላት በቀላሉ ተደራሽ ሊያደርግ የሚችል ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

98. ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ፡-

- ✓ የሚያስተዳድራቸውን መንገዶች በተመለከተ ያለውን መረጃ ለመያዝና በቀላሉ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል የሌለው መሆኑ፣
- ✓ ድልድዮችን በተመለከተ ግን ሶፍትዌር (Bridge Management System) (BMS) ያለ ቢሆንም ሶፍት ዌሩ ዌብ ቤዝድ ባለመሆኑ (በኢንተርኔት ያልተገናኘ በመሆኑ) ከዲስትሪክቶች ጋር መረጃ በቀላሉ ለማቀናጀት የማያስችል መሆኑ፣
- ✓ በየባለሥልጣኑ ዲስትሪክቶች መንገዶች የእይታ የዳሰሳ ጥናት በየጊዜው የሚከናወን ቢሆንም (Integrated) ሲሰተም ባለመሆኑ መረጃዎቹን ወቅታዊ ለማድረግ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ✓ የመንገድ መረጃን ለማግኘት ለሚፈልግ ማንኛውም አካል ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት (ሲሰተም) የሌለ መሆኑ፣
- ✓ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸውን መንገድን በተመለከተ ያለውን መረጃ ለመያዝና በቀላሉ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያስችል ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል የሌለው መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል፡፡

99. ስለሁኔታው የመንገዶች ባለሥልጣን ኃላፊዎች ተጠይቀው ፡-

- ✓ የድልድይ አስተዳደር ሥርዓቱ (BMS) ከዲስትሪክቶች ጋር በኮምፒውተር የተቀናጀ ሲሆን በድህረ ገጽ ላይ ተመሠረተ /ዌብ ቤዝድ/ ለማድረግ ለዚህና የመንገድ ሀብት አጠቃላይ አሠራር ለማዘመን በተቀጠረ የግል አማካሪ አማካይነት ይህን እና ሌሎችንም ሶፍትዌሮች በማቀናጀት አዲስ

ሥርዓት/የመንገድ ሃብት አስተዳደር ሥርዓት/ ለመዘርጋት ሥራው እየተጠናቀቀ መሆኑ፣

- ✓ እስከ አሁን ባለው ሁኔታ መረጃዎች በተለያየ ቦታዎች ማለትም በመንገድና በድልድይ አስተዳደር ሥርዓት መረጃ ቋት /ዳታ ቤዝ/ ውስጥ ያሉ ሲሆን ይህንን ዘመናዊ በሆነ መልኩ ለማከናወን በአፍሪካ ልማት ባንክ የገንዘብ ድጋፍ የተቀጠረው አማካሪ ሥራውን በማጠናቀቅ ላይ በመሆኑ እነዚህን በአንድ ላይ በማቀናጀት እና በአንድ አሠራር ሥርዓት በማድረግ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ለመዘረጋት የታሰበ መሆኑ፣
- ✓ መረጃዎችን ወቅታዊ የማድረጉ ሁኔታ አዲስ በሚዘረጋው የተቀናጀ የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ ሲደረግ አብሮ የሚከናወን መሆኑ፣ በተጨማሪም የተለያዩ መረጃዎችን በባለሥልጣኑ ድረገጽ/ዌብ ሣይት/ ስለሚጫን እዚያ ላይ ማግኘት የሚቻል መሆኑን፣

በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact Sheet) ላይ በሰጡት አስተያየት ላይ ገልፀዋል፡፡

100. የድልድይ አስተዳደር ሥርዓቱ (BMS) የተቀናጀ ለማድረግና የመንገድ ሀብት አጠቃላይ አሠራር ለማዘመን በተቀጠረ የግል አማካሪ አማካይነት ሶፍትዌሮች በማቀናጀት አዲስ የመንገድ ሃብት አስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋት ሥራው እየተጠናቀቀ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ይህንን የሚያሣይ ማስረጃ ያለቀረበ በመሆኑ የተሰጡት ምላሾችን ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

101. የመንገዶችና የድልድዮችን ታሪክ የሚይዝ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከልና መረጃውን ለሚፈልጉት አካላት በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ካልተደረገ መንገዶችንና ድልድዮችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማስተዳደር አስቸጋሪ ከማድረጉም በተጨማሪ መዋለ ንዋያቸውን በሀገሪቱ ውስጥ ለማዋል ለሚፈልጉት ባለሀብቶች እና በመንገድና ድልድዮች ጥገና ሥራ ላይ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ የሥራ ተቋራጮች መረጃውንም በቀላሉ ለማግኘት አስቸጋሪ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ (Conclusion)

102. የመንገዶችና የድልድዮች ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት በየዓመቱ መከናወኑን እና በየዓመቱ የሚታቀዱት የጥገና እቅዶች በተያዘላቸው በጀት፣ ጥራትና ጊዜ እየተጠናቀቁ መሆኑን በተመለከተ፡-

- የመንገዶችና የድልድዮች ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት በዕቅዱ መሰረት በተሟላ ሁኔታ አለመከናወኑ፣
- የድልድዮች ጥገናን በተመለከተ በስትራቴጅክ ዕቅድ ውስጥ ተካቶ ያልታቀደ መሆኑ፣
- የመንገድና የድልድይ የጥገና ዕቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ የማይጀመሩ፣ በተመደበላቸው በጀት፣ ጥራትና ጊዜ የማይጠናቀቁ መሆኑ፣
- የአዳማ አሰላ አስፋልት መንገድ በ2008 ዓ. ም ድንገተኛ ጥገና ቢከናወንም መንገዱ በጎርፍ ተቆርጦ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፣
- የአዳማ አሰላ አስቸኳይ መንገድ ጥገናው ከተጠናቀቀ በኃላ የኮንትራት ውል የተፈረመ መሆኑ፣
- ለግል ኮንትራክተሮች የተሰጡ የመንገድ ጥገና ፕሮጀክቶች የመንገድ ጥገና ሥራ ክንውንና ጥራት በተፈለገው ደረጃ እየተከናወነ አለመሆኑ፣
- የመንገዶችና ድልድዮች ሊስተናግዱት ከሚገባው የክብደትና የትራፊክ ፍሰት በላይ የሚያስተናግዱ መሆኑን፣
- መንገዶች መሸከም ከሚችሉት የክብደት መጠን እና የትራፊክ ፍሰት በላይ የሚያስተናግዱበት ሁኔታ መኖሩ፣
- የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን ከመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ስራ ጋር የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ በዕቅድና በኮንትራት ውል ውስጥ ተካቶ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመደበኛና ወቅታዊ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነዱ መሰረት ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ውል መዋዋል ቢኖርበትም ያለውል የሚያሰራ መሆኑ፣

- የግል ሥራ ተቋራጮችም በገቡት ውል መሰረት የመንገድ ጥገናውን የማያጠናቀቁ መሆኑን

- የመንገድ ተጠቃሚው ህብረተሰብ በመንገድ ሀብት አስተዳርና ጥገና ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት አለመከናወኑ፣ የመንገድ ተጠቃሚው ህብረተሰብ በመንገድ ጥገና ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅና የእርካታ ዳሰሳ ጥናት በመከናወን ችግሮችን በመለየትና ለማስተካከል ያልተሠራ መሆኑ፣

- ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ፈጣን የሆነ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል መዋቅር (አደረጃጀት) ወይንም የተዘረጋ ሥርዓት የሌለው መሆኑ፣
- በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች የሚጠየቁበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ፣
- መንገዶችን ላቫ ያጅ፣ መገበያያ፣ የግንባታ ቁሳቁስ ማከማቻ እና ማዘጋጃ ሆኖ ለተሽከርካሪ አደጋ በሚያጋልጥ መልኩ የሚገኝ መሆኑ፣
- በመንገዶችና በድልድዮች ላይ የሚተላለፉ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ለማስከበር አጥፊዎች በመንገዱ ላይ ባደረሱት ጥፋት ልክ ለመጠየቅ የሚያስችል መመሪያ የሌለ መሆኑ፡-
- መንገዶች ከሚያልፉባቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት/ እንዲከናወን ያልተደረገ መሆኑ.
- መንገድን በተመለከተ ያለውን መረጃ ለመያዝና በቀላሉ ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ የሚያችል ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል የሌለው መሆኑ፣
- ድልድዮችን በተመለከተ ግን ሶፍትዌር (Bridge Management System) (BMS) ) ያለ ቢሆንም ሶፍት ዌሩ ዌብ ቤዝድ ባለመሆኑ (በኢንተርኔት ያልተገናኘ በመሆኑ) ከዲስትሪክቶች ጋር መረጃ በቀላሉ ለማቀናጀት የማያስችል መሆኑ፣

103. ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች እና ግድፈቶች በብቃት፣ ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሀገሪቱን የመንገድ አውታር ደረጃ ኢና መጠን ከማሳደግ አኳያ፣ እንድሁም በየጊዜው ኢየጨመረ የመጣውን የመንገድ አውታር በአግባቡ

ከመጠበቅና ከመጠቀም አንጻር ትኩረት ኢንድደረግ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

104. የመንገዶችና ድልድዮች የተለያየ የጥገናና እንክብካቤ ሥርዓት ተከትለው እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡


- የመንገዶችና የድልድዮች ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት(Condition Servey) እንደየመንገዱ ደረጃ፣ የመሬትና የአየር ንብረት (ፀባይ) ሁኔታ የዳሰሳ ጥናት በዕቅድ ላይ ተመስርቶ መከናወን እንዳለበት እና እንደየ ጉዳት ደረጃቸው መስፈርትና ቅደም ተከተል በማዘጋጀት መንገዶችም ሆነ ድልድዮች ለከፋ ጉዳት ሣይደረጉ በወቅቱ ጥገናና እንክብካቤ እንዲያገኙ በማድረግ የመንገድ ሀብት በአግባቡ በመጠበቅ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት አስታዋፅኦ እንዲያበረክት ሊደረግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የጥገና ዕቅድ ሲያዘጋጅ ያሉትን ድልድዮች ከግምት ውስጥ በማስገባትና ትኩረት በመስጠት በስትራቴጂክ ዕቅዱ ውስጥ በማካተትና በዓመታዊ በማከፋፈል ተገቢውን የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ተገነንብቶ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ወደ መንገድ ሀብት የገቡ መንገዶችና ድልድዮች እንደሚያስተናግዱት የትራፊክ ፍሰት መጠን እና የሚስተናግዱት የክብደት መጠንን ከግምት ያስገባ ክትትል በማድረግ ሲገነቡ ታሳቢ የተደረጉ የአገልግሎት ዓይነትና ጊዜ እንዲሰጡ አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያገኙ ሊደረግ እንዲሁም መደበኛ ጥገና በሚመደብላቸው በጀት፣ ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ መንገዱም ሆነ ድልድይ የጉዳት መጠን ተባብሶ ለመንገድ ግንባታ የሚውለውን የሃገሪቱን ሀብት ሣይጎዳ ሊጠበቅ ይገባል፡፡
- የመንገድ ዳር ምልክቶች፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶች የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ የሚረዱ በመሆናቸው የመንገዱም ሆነ የድልድዮች ጥገና በሚታቀዱበትም ሆነ ውል በሚገባበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸውና አብረው እንዲታቀዱ በማድረግ የትራፊክ አደጋ ለመቀነስ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ሊደረግ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ እንደየ ሥራው ባህሪይ ብቃት ያላቸው የሥራ ተቋራጮችን ለማግኘት የሚረዳ ግልፅ የሆነ የቴክኒክ መምረጫ መስፍርትና መመሪያ በማዘጋጀት እና በሚመለከታቸው አካላት በማፀደቅ ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ በተቋራጮች አቅም ውስንነት የሚፈጠረው የሥራ ጥራትና መጓተት ሊቀርፍ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድና ድልድይ ጥገናን በተመለከተ የሚመራባቸው መመሪያዎች በማዘጋጀትና በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግ የመንገድ ጥገና እና እንክብካቤ በዘመናዊ አሠራር እንዲታገዝ ሊያደርግ
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን ጋር በተፈራረመው የመግባቢያ ሰነድ መሰረት ለኮርፖሬሽኑ ለሚሰጣቸው እያንዳንዱ የጥገና ሥራዎች ውል ሊዋዋልና ግልጽ የሆነ የተጠያቂነት ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች ጊዜ የማይሰጡና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚፈልጉ በመሆናቸው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ይህንን ለማድረግ የሚያስችል የአደረጃጀት ወይንም ሥርዓት በመዘረጋት ችግሮች ወቅታዊ ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ በማመቻቸት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎችን ለመከላከል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀትና ከሚመለከታቸው የአካባቢ መስተዳደሮች ጋር የጋራ ግንዛቤ በመያዝ የመንገድ ሀብት የሚጠበቅበት ምቹ ሁኔታ ሊኖር ይገባል፡፡
- የመንገድ ሀብት ለመጠበቅ እንዲረዳ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ ለማስከበር እየተዘጋጀ ያለው ደንብ ከመዘግየትም አልፎ የተረሳ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት በመስጠት ደንቡ ተጠናቆ በመንገድ ሀብት ላይ የሚደረሰውን ጉዳት ለመከላከል እንዲያስችል አፋጣኝ የመፍትሔ እርምጃ በመውሰድ ከክብደት ጋር ተያይዞ በመንገድ ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሊቀንስ ይገባል፡፡
- መንገዶች በውሃ አካላት እንዳይጎዱ መንገዱ ከሚያልፉባቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት/ በማከናወን በውሃና በመሬት መንሸራተት የሚከሰቱ የመንገድ ብልሽት ሊቀንስ ይገባል፡፡

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገዶችና የድልድዮችን መረጃ የሚይዝ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል በማዘጋጀት እና መረጃዎችን በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግ መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

105. በመጨረሻም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ በናሙና ተመርጠው የታዩ የባለሥልጣኑ ቅ/ዳይሬክተሬቶች፣ አማካሪ ድርጅቶች እና የግልሥራ ተቋራጮች የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት የተጠየቁትን መረጃዎች በወቅቱ በማቅረብና ለቀረቡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ስለተደረገልን የሥራ ትብብር ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አባሪ 1 Road Asset Management DDG



# አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

| የኦዲት ጭብጥ /Issues/ | የመገምገሚያ መስፈርት /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. መንገዶች ከተገነቡ በኋላ ለረዥም ጊዜ ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ ጥበቃ፣ ጥገና እና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑን መገምገም፣ | 1.1ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድራቸውን መንገዶች ሁኔታ የሚመለከት ጥናት በየዓመቱ ሊያከናወን ይገባል፡፡ ምንጭ፡ Technical maintenance Page 5 |
| | 1.1 ባለስልጣን መ/ቤቱ በየዓመቱ የሚያቅዳቸው የመንገድ ድልድይ ጥገና እቅዶች በተያዘላቸው በጀት፣ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡ ማዕቀፍ የተዘጋጀ ስትራቴጂ ዕቅድ (2008-2012 ዓ.ም) ገፅ 23 |
| | 1.2 ባለሥልጣን መ/ቤቱ መንገዶችና ድልድዮች የሚያስተናግዱትን የትራፊክ መጠን፣ የአባቢ አየር ሁኔታ እና መሬት አቀማመጥ መሰረት በማድረግ በየዓመቱ መደበኛ የጥገና አገልግሎት እንዲያገኙ በዕቅድ ላይ ተመሰርቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡ (Pavement Rehabilitation and Asphalt over Lay manual page 5) |
| | 1.3የተጎዱ የመንገድ ዳር ምልክቶችን፣ የመንገድ ቀለሞችንና ምልክቶችን ከመንገድ ጥገና ስራ ጋር ተካቶ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ |
| | 1.4 ባለሥልጣኑ የመንገድ ጥገና የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች የሚመረጡበት ግልጽ መመሪያና መስፈርት አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ |
| | 1.5ባለሥልጣኑ የመንገድና ድልድይ ጥገናን በተመለከተ የሚመራባቸው መመሪያዎች በማዘጋጀትና በቦርድ በማፀደቅ ሥራ ላይ ሊያውል ይገባል፡፡ ምንጭ፡- የባለሥልጣኑ መቋቋሚያ ደንብ 247/2003 ዐንቀፅ 8/2 |
| | 1.6ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራ ውሎቹን በማዘጋጀት ሥራዎች በውሉ መሠረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በበላይነት ሊቆጣጠር ወይም በሌላ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ሊያደርግ ይገባል፡፡ ምንጭ፡ የባለሥልጣኑ መቋቋሚያ ደንብ 247/2003 ዐንቀፅ6/7 |
| | 1.7 ባለስልጣኑ የመንገድ ተጠቃሚው ህብረተሰብ በመንገድ ጥገና ላይ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት በማከናወን እርካታቸው እንዲጨምር ሊሠራ ይገባል፡፡ ምንጭ፡- በውጤት ተኮር ሥርዓት (BSC) ማዕቀፍ የተዘጋጀ ስትራቴጂ ዕቅድ (2008-2012ዓ.ም) ገፅ 22 |

| | |
|---|---|
| | 1.8 ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለድንገተኛ/አስቸኳይ/ የመንገድና ድልድይ ጥገና ሥራዎች በራስ ኃይል ፈጣን የሆነ ምላሽ የሚሰጥበት ሥረዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡ ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ |
| | 1.9 በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም በመንገዶች ላይ ማናቸውም መሰናክሎች የሚያስቀምጡ ወይም ነዳጅና ቅባት ነክ ፈሳሾችን የሚያፈሱ ሰዎች አግባብ ባለው ህግ መሠረት እንዲጠየቁ ለማድረግ የሚያግዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡<br>**ምንጭ የባለሥልጣኑ መቋቋሚያ አዋጅ 247/2011 ዐንቀፅ 6/21** |
| | 1.10 የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንቦችን ለማስከበር የአፈፃፀም መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡<br>**የባለሥልጣኑ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 247/2003 አንቀፅ 6/11** |
| | 1.11 የመንገድ ሀብት ለመጠበቅ እንዲረዳ የተሽከርካሪ መጠንና ክብደትን (ትርፍ ጭነትን) ደንብ መሰረት ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-በ2008-2012 ውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ 2** |
| | 1.12 ባለስልጣኑ ከመንገድና ድልድይ ጥገና ኮንትራክተሮች ጋር በገባው ውል መሠረት ግዴታውን ካልተወጣ የሚጠየቅበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ መልካም ተሞክሮ** |
| | 1.13 ባለስልጣኑ በመንገድ ጥገና ወቅት በተፈጥሮ አካባቢና በህብረተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በጥናት በመለየት የሚቀንስበትን መፍትሔዎች በማስቀመጥ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡<br>**ምንጭ፡- በውጤት ተኮር ስርዓት(BSC) ማዕቀፍ የተዘጋጀ ስትራቴጂ ዕቅድ (2008-2012 ዓ.ም) ገፅ 22** |
| | 1.14ባለስልጣኑ የሚያስተዳድራቸው መንገዶች ከሚያልፉባቸው የመስተዳድር አካላት ጋር በመቀናጀት የአካባቢ ጥበቃ/የአረንጓዴ ልማት ሊያከናወን ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- በውጤት ተኮር ስርዓት(BSC) ማዕቀፍ የተዘጋጀ ስትራቴጂ ዕቅድ (2008-2012 ዓ.ም) ገፅ 17** |
| **1.1 ድልድዮች ከተገነቡ በኋላ ተፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ የድልድዮችን ታሪክ(መረጃ) በተሟላ** | 2.1 ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድራቸውን ድልድዮች ያለበት ሁኔታ የሚመለከት ጥናት በየዓመቱ ሊያከናወን ይገባል፡፡<br>**ምንጭ:** Technical maintenance Page 5 |
| | 2.2 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የድልድይ ጥገናን በተመለከተ ስትራቴጅክ ዕቅድ ሊያዘጋጅና በዓመታዊ ዕቅድ በመከፋፈል ሊተገብር ይገባል፡፡<br>**ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |

| | |
|---|---|
| መልኩ በመያዝ ጥበቃ፣ ጥገና እና እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑን መገምገም፣ | 2.3 የድልድዮች ጥገና እንደ እድሚያቸውና እንደ ጉዳት መጠናቸው ቅደም ተከተል ወጥቶላቸው የሚጠገኑበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ** |
| | 2.4 በድልድዮች ላይ የሚተላለፉ ተሽከርካሪዎች የክብደት መጠን ተወሰኖ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 2.5 አንድ ድልድይ ከመጠገኑ በፊት በተቋራጩ ለጥገና የሚውሉ ግብዓቶች የጥራት ክትትል ማረጋገጫ በአማካሪ ድርጅቶች/በራስ ኃይል/ ሊሰጥ ይገባል። **ምንጭ የውጭ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት 2004 ዓ.ም ገጽ 18** |
| | 2.6 ባለስልጣን መ/ቤቱ በየዓመቱ የሚያቅዳቸው የድልድይ ጥገና እቅዶች በተያዘላቸው በጀት፣ጥራትና ጊዜ እንዲጠናቀቁ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል። **ምንጭ፡ ማዕቀፍ የተዘጋጀ ስትራቴጂ ዕቅድ (2008-2012 ዓ.ም) ገፅ 23** |
| | 2.7 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸውን የድልድዮችን ታሪክ የሚይዝ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል ሊኖረው ይገባል። **ምንጭ፡- 2008-2012 በውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ 41** |
| | 2.8 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸው ድልድዮችን በተለከተ የሚይዛቸው መረጃዎች በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል። **ምንጭ፡- 2008-2012 በውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ 23** |
| 1 **ዘመናዊ፣ የተቀናጀና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመጠቀም ለሚፈልገው ተገልጋይ በብቃት እና በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል እንዲሁም ቅንጅታዊ የአሰራር ስረዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ።** | 3.1 ለእያንዳንዱ መንገድና ድልድይ ጥገና የኮንትራት ውል ሊዘጋጅላቸውና ውሎቹ ተደራጅቶ ሊያዙ ይገባሉ። **ምንጭ፡- የመግባቢያ ሠነድ ገጽ 2 ተ.ቁ 3.4** |
| | 3.2 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸውን የመንገዶች ታሪክ የሚይዝ ዘመናዊ የመረጃ ማዕከል ሊኖረው ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- 2008-2012 በውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ 41** |
| | 3.3 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸውን መንገዶች መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈና መረጃውን ለሚፈልጉ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የሚሆንበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- 2008-2012 በውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ 23** |
| | 3.4 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚያስተዳድራቸው መንገዶችን በተመለከተ የሚይዛቸው መረጃዎች በየጊዜው ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡**ምንጭ፡- 2008-2012 በውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ 23** |
| | 3.5 ባለስልጣኑ ከባለድርሻ አካላት የሚቀርቡ የመረጃ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችል ግልፅና ተጠያቂነት የሰፈነበት የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት ወቅታዊ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ **ምንጭ፡- 2008-2012 በውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ** |

| | | |
|---|---|---|
| | | ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ 23 |
| | 3.6 | ባለስልጣኑ ለክልል የመንገድ ባለሥልጣኖች የመንገዶችና ድልድዮች ጥገናን በሚመለከት የቴክኒክ ድጋፎችን እንዲያገኙ በማድረግ የመፈፀም አቅማቸውን እንዲያሻሽሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** 2008-2012 **በውጤት ተኮር ሥረዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ** 21 |
| | 3.7 | ከክብደት በላይ መተላለፍን የሚመለከቱ መረጃዎች ተጠናቅረው ሊያዙ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- ከ** 2008-2012 **ውጤት ተኮር ሥርዓት የተዘጋጀ ስትራቴጅክ ዕቅድ ገጽ** 23 |
| | 3.8 | ባለሥልጣኑ ከመንገድና ድልድይ ጥገና ጋር በተያያዘ በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች በተሰጡ የኦዲት ግኝት ሪፖርቶች ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የባለሥልጣኑ መቋቋሚያ ደንብ** 247/2003 **አንቀፅ** 8/3 |

## አባሪ 3፡ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ ኔትወርክ ማኔጅመት ዳይሬክቶሬት የፊዚካል ስራ አፈፃፀም እስከ መስከረም 30 2011ዓ.ም

Ethiopian Roads Authority Road Asset Projects progress RNMMCABD as of September 30, 2018

| I. N | የፕሮጀክቱ ስም (Project Name) | የጥናው አይነት | የስራ ተቋራጭ/ አማካር ድርጅት (Contractor/ Consultant | የሚጠገንነው መንገድ ርዝመት ኪ.ሜ (Contract Length, Km) | ከንትራቱ የምወስደው ቀን Contract Duration (days) | | የኮንትራት ዋጋ Contract Amount (ETB) | የኮንትራት ውል የተፈረመበት ቀን Contract signing date | ስራው የምጀም ርበት ቀን Commencement Date | ስራው የምያልቅበት ቀን Completion Date | | ስራው አሁን ያለበት ደረጃ Progress to Date (%) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | Original ትክክለኛ | Revised የተከለሰ | | | | Original ትክክለኛ | Revised የተከለሰ | |
| 1 | ሻሻማኔ ዲስትርክት | | | | | | | | | | | |
| | ✓ መቂ-ሻሻመኔ-ሐዋሳ | ከባድ ጥገና | ዮናታን አብዬ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ | 146 | 730 | 820 | 197,170,298 | 11-may-16 | 22-jun-18 | 23-sep-18 | 21-sep-18 | 1% |
| | ✓ አሰላ-ቦቆጅ-ዶዶላ | ጥቃቅን ጥገና | ናትኮን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ/ሻሻማኔ | 120 | 730 | - | 43,868,112 | 6-nov-17 | 15-nov-17 | 6-nov-19 | - | 9% |
| | ✓ ዴሎመና-ብድሬ | Paving town section | ሎቱሰ ኮንስትራክሽን ኃ/የ/የግ/ማህበር | 3 | 365 | 508 | 14,999,234 | 31-may-16 | 22-jun-17 | 21-jun-17 | 11-des-17 | 9% |
| | - | 4 ጥቃቅን፣2 ወቅታዊና 1 ከባድ ጥገና | ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን/ | 986 | 365 | - | 169898175 | - | 7-jul-18 | 8-jul-18 | - | 4% |
| 2 | ድሬደዋ ዲስትርክት | | | | | | | | | | | |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ✓ ኪ.ሜ145-ኪ.ሜ 220(ኮንት.3) | አስፓልት ጥገና(Asphalt overlay) | ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን/ ድሬደዋ | 75 | 730 | - | 458,954,871 | 26-may-16 | 22-jun-16 | 21-jun-18 | - | 51.67% |
| | ✓ ኪ.ሜ220-ማል (ኮንትራት.4) | አስፓልት ጥገና (Asphalt overlay) | DCE/GOGO T/in JVRoad Design | 73.96 | 730 | 790 | 381,830,205 | 26-may-16 | 22-jun-16 | 21-jun-18 | 31-Aug-18 | 55.10% |
| 3 | **ጅማ ዲስትርክት** | | | | | | | | | | | |
| | ✓ አጋሮ-ግራ | የከተማ መንገድ ንጣፍ Paving Town section | ዊትነስ የግንባታ ኢተርፒራይ ዝ/ጅማ | 2.5 | 365 | - | 21,414,202 | 9-may-16 | 9-jun-16 | 9-jun-17 | - | 6.5% |
| | ✓ ሳጃ-ፎፋ | የከተማ መንገድ ንጣፍ Paving Town section | ዊትነስ የግንባታ ኢተርፒራይ ዝ/ጅማ | 3 | 365 | - | 17,918,999 | 9-may-16 | 9-jun-16 | 9-jun-17 | - | 0% |
| 4 | **ሶዶ ዲስትርክት** | | | | | | | | | | | |
| | ✓ ሲሌ የድልድይ ጥገና | ሲሌ ድልድይ | ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን/ሶዶ | - | 365 | 455 | 45,635,472 | 29-oct-15 | 18-jun-16 | 17-jul-17 | 15-oct-17 | 0% |
| | ✓ ሶዶ-ሰላም በር | የከተማ መንገድ ንጣፍ Paving Town section | ዳይናሰል ኢንጅነርግ/ ሶዶ | 5 | 365 | 820 | 19,354,194 | 22-Aug-16 | 14-Oct-16 | 14-Oct-17 | 13-Dec-18 | 22% |
| 5 | **ዓለምገና ዲስትርክት** | | | | | | | | | | | |
| | ✓ አዳማ-አሰላ | የዉሀ መውረጃ ሥራ/Drainage Works | ሻርፒኮን ኮንስትራክሽን/ኃ/የ/የግ/ማ | - | - | - | 53,379,153 | 20-Oct-16 | 23-Mar-17 | 13-nov-18 | 26-May-19 | 62% |
| 6 | **ጎንደር ዲስትርክት** | | | | | | | | | | | |
| | ✓ ደልግ-ቹሀት(delgi-chuahit) | የከተማ መንገድ ንጣፍ Paving Town section | እዮብ ሙሉጌታ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን /ጎንደር | 1.7 | - | - | 8,370,958 | 2-jun-16 | 17-jun-16 | 17-jun-17 | 2-mar-18 | 11% |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ✓ ጋሳይ-ሰማዳ (Gasay-Semada) welelbair | የከተማ መንገድ ንጣፍ Paving Town section | አመሃ አለሙ ጠቅላላ ኮንስትራክሽን /ጎንደር | 2.3 | - | - | 7,828,535 | 2-jun-16 | 17-jun-16 | 17-jun-17 | 1-mar-18 | 19% |
| 7 | ኮምቦልቻ ዲስትርክት | | | | | | | | | | | |
| | ✓ መካነሰላም ከተማ | Widening | ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን/ ኮምቦል | 2.80 | - | - | 49,845,805 | 31-Dec-16 | 24-Jan-17 | 24-jan-18 | - | 26.3% |
| | ✓ Alakel & Ambedom ድልድይ | ድልድይ | ቴድሮስ ኒቆድሞስ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ/ ኮምቦልቻ | - | 270 | - | 8,319,684 | 14-Nov-16 | 30-Nov-16 | 27-Aug17 | - | 51.18% |
| | ✓ የዓዋሽ ድልድይ ተንዳሆ ስኳር ፋብርካ | ድልድይ | ኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ስራዎች ኮርፖሬሽን/ ኮምቦል/ ECDSWC | - | 365 | - | 67,847,576 | 26-Apr-16 | 15-Oct-16 | 15-Oct-17 | - | 0% |
| 8 | ደ/ማርቆስ ዲስትርክት | | | | | | | | | | | |
| | ✓ ዱርብቴ-ሻሁራ ቁንዝላ | የከተማ መንገድ ንጣፍ Paving Town section | ቢሌን ወ/ዮሀንስ ጠቅላላ ተቋራጭ/ ደ/ማርቆስ | 2 | 365 | - | 9,171,147 | 4-May-16 | 2-Jun-16 | 2-Jun-17 | - | 21% |
| | ✓ ዱርብቴ-ሻሁራ ✓ ላልበላ | የከተማ መንገድ ንጣፍ Paving Town section | ቢሌን ወ/ዮሀንስ ጠቅላላ ተቋራጭ/ ደ/ማርቆስ | 25 | 365 | - | 11,311,843 | 4-May-16 | 2-Jun-16 | 2-Jun-17 | - | 24% |